የፌደራል የሥነምግባር እና
የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

FEDERAL ETHICS AND
ANTI-CORRUPTION COMMISSION

የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ

አጥኚዎች፡

ኢማኑኤል ገብረዮሐንስ (ዶ/ር)

መኮንን ቦጋለ (ዶ/ር)

ለታ ሴራ (ዶ/ር)

አሰፋ መኮንን (ዶ/ር)

ሰኔ 2014

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የጥናቱ አጭር ማጠቃለያ (Executive Summary)

ሙስና በሁሉም የአንድ ሀገር ዘርፎች ውስጥ በመከሰት በሀገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በማስከተል ሀገር እንደሀገር በማይቀጥልበት ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል ወይም ተቋማትን የማፍረስ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አደገኛ የሆነ የወንጀል አይነት ነው። ኢትዮጵያም በዚህ ወንጀል ከተጎዱ ሀገራት አንዷ በመሆኗ የፌደራል የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይህንን ብልሹ አሰራር ጥናትን መሰረት ባደረገ መልኩ ለመከላከል የመሪነት ሚና ተሰጥቶት በመስራት ላይ ይገኛል። ይህ ጥናትም ከተግባሮቹ አንዱ ሲሆን ዋና ዓላማውም በገቢዎች ዘርፍ ሥር ባሉ ተቋማት (በገቢዎችና ጉምሩክ) ውስጥ የሙስና ስጋት ጥናት በማካሄድ ሙስናን ለመቀነስ ምክረ-ሃሳብ መስጠት ነው። ጥናቱ አላማ ተኮር በመሆኑ ትኩረቱ በፌደራል ደረጃ የሚመሩ የገቢዎችና ጉምሩክ መስሪያ ቤቶች እና በሁለት ክልሎች በኦሮሚያና በደቡብ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ በተመረጡ የዘርፉ ተቋማት ላይ ነው።

ጥናቱ ገላጭ (descriptive) ሲሆን አቀራረቡ ቅይጥ (አሀዛዊ እና ዓይንታዊ) ዓይነት ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች በአላማ ተኮር የጥናት አይነት የተመረጡ በዘርፉ ሥር ባሉ ተቋማት የስራ ሂደቶች ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛ የአስተዳደር አባላት እና እንደ ታክስ ኦዲት፣ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት፣ ታክስ አወሳሰን፣ ታክስ አሰባሰብ፣ ህግ ክፍል፣ የውስጥ ኦዲት፣ ግዥ፣ የሰው ሃብት፣ ወዘተ የሚሰሩ ሰራተኞች ናቸው። ለጥናቱ የመጀመርያ ደረጃ መረጃ የተሰበሰበው በመጠይቅ፣ በሀሳብ ማጎልበቻ ዉይይት (brainstorming) እና በቃለ-መጠይቅ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ደግሞ ከተለያዩ ሰነዶች ተሰብስበዋል። መረጃዎቹን ለመለየት፣ ለመተንተንና ለመገምገም ባለ አምስት ደረጃ ስታንዳርድ የሙስና ስጋት ጥናት ማካሄጃ ንድፈ-ሀሳብ ተጠቅመናል። ደረጃዎቹም ሁኔታዎችን መረዳት፣ የሙስና ስጋቶችና ብልሹ አሰራሮችን መለየት፣ ስጋቶችን መተንተንና መገምገም እና ምክረ ሀሳብ መስጠት ናቸው።

እነኚህን የጥናት መንገዶች በመጠቀም የተለያዩ የሙስና አይነቶችና ብልሹ አሰራሮች ተለይተዋል። ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመለየት በተደረገ ትንተናና ግምገማ ከጉምሩክ ንዑስ-ዘርፍ የዋጋ አተማመን መመሪያን መሰረት ያላደረገ ዋጋ መወሰን፣ ዕቃዎችን የታሪፍ አጣጣል መመሪያን ያላማከለ ታሪፍ ላይ መመደብ፣ ታክስ ያልተከፈለባቸው ዕቃዎች ከህጋዊዎቹ ጋር ተቀላቅለው ወደ ሀገር መግባት/መውጣት፣ እንዲሁም ሰነድ አልባ እና ገደብ/ክልከላ የተደረገባቸውን ዕቃዎች በመመሳጠር በኬላ ማሳለፍ፣ በገቢዎች ንዑስ-ዘርፍ ደግሞ በስልጣን አላግባብ መገልገል፣ ጉቦ መቀበል፣ የመንግስታዊ/ህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት (በሃሰተኛ ሰነድ መገልገል)፣ እና ያላግባብ ጉዳይን ማጓተት የመከሰት እድላቸው እንዲሁም ከተከሰቱ የሚያስከትሉት ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል።

የክትትልና ቁጥጥር ሂደት በሚፈለገው ደረጃ ያለመጠናከር፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የቅንጅት ክፍተት፣ የስራ ብዛትና ያለው የሰው ሀይል አለመመጣጠን፣ የሰራተኞች እውቀትና ክህሎት ማነስ፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በመደበኛና በበቂ ሁኔታ አለመኖር፣ የሰራተኞች የስነ-ምግባር ጉድለት፣ የአንዳንድ ስራዎች በሲስተም (በቴክኖሎጂ) የተደገፈ አለመሆን፣ እንዲሁም የስነ-ምግባር ጥሰቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለህግ የማቅረብ እና የክስ ስርአት መላላት (weak law enforcement and prosecution) ለብልሹ አሰራሮች መከሰት እንደ ምክንያት ተለይተዋል።

የገቢዎች እና ጉምሩክ ተቋማት በጥናቱ የተለዩትን የሙስና ስጋት መከሰት መንስዔዎች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የቁጥጥርና ክትትል ስርዓትን የማጠናከር፣ ለአመራሮችና ሠራተኞች ጥራትና ተገቢነት ያለዉ የስነ-ምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበቻ ሥልጠና መደበኛ የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ የመስጠት፣ አደጋው ከመከሰቱ በፊት ሪስክን መሰረት ያደረገ የመከላከል ስራ የመስራት፣ የባለሙያዎችን የሙያ ክህሎት በመደበኛ እና ወቅታዊ ስልጠና የማሳደግ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት የመዘርጋት እና የመተግበር፣ እንዲሁም የጥፋት ባህሪዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አብሮ በመስራት የእርምት እርምጃዎችን የመወሰንና የመተግበር ስትራተጂ ቀርፀው ሙስና ስጋት እንዳይሆን የመከላከል ስራ እንዲሰሩ ጥናቱ ይመክራል።

"I have been impressed with the urgency of doing.
Knowing is not enough; we must apply.
Being willing is not enough; we must do."

Leonardo da Vinci

"በአጣዳፊነት ስራን መስራት ደስ ያሰኘኛል።
ማወቅ በቂ አይደለም፣ መተግበር አለብን።
ፈቃደኛ መሆን በቂ አይደለም፣ ማድረግ አለብን።"

ሊዮናርዶ ዳ ቪንቺ

ማውጫ (Contents)

የጥናቱ አጭር ማጠቃለያ (Executive Summary) 1

ክፍል 1፡- መግቢያ (Introduction) 4

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the Study) 4

1.2. የጥናቱ ዓላማዎች (Objectives of the Study) 6

1.2.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ 6

1.2.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች 6

1.3. የጥናቱ ፋይዳ (Significane of the Study) 7

1.4. የጥናቱ ወሰን (Scope of the Study) 7

1.5. የጥናቱ ውስንነት (Limitations of the Study) 7

ክፍል 2፡- የጥናቱ ስነ-ዘዴ 8

2.1. የጥናቱ ቦታ (Study Area) 8

2.2. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design) እና አቀራረብ 8

2.3. የጥናቱ ተሳታፊዎች (Study participants) 8

2.4. የናሙና ስብጥር (Distribution of Sample Respondents) 9

2.5 የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች 10

2.6 የጥናቱ የትንተና እና ግምገማ ዘዴ 11

ክፍል 3፡- የሙሰና ስጋት ጥናት የንድፈ ሃሳባዊ ሞዴል 13

3.1. ስለጥናቱ አጠቃላይ ግንዛቤ ማሳደግ እና ተሳታፊዎችን መለየት (1ኛ) 13

3.2. የተቋሙን የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት መለየት (2ኛ) 13

3.3 የተቋሙን የሙስና ስጋቶች መተንተን (3ኛ) 14

3.4 የተቋሙን የሙስና ስጋቶች መገምገም (4ኛ) 15

3.5 የሙስና አደጋዎችን ለማከም የመፍትሔ ሀሳብ ማዘጋጀት (5ኛ) 16

ክፍል 4፡- የሙስና ስጋት ልየታ፣ ትንተና እና ግምገማ 17

ክፍል 5፡- የጥናቱ ግኝቶች ማጠቃለያ (Summary) 34

ማጣቀሻዎች (References) 42

አባሪ (annex)፡ በዳሰሳ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ትንተና 43

ክፍል 1፡- መግቢያ (Introduction)

የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስና በተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት ላይ ያለበትን ሁኔታ ለመረዳት እንዲያግዘው የሙስና ስጋት ጥናት እያካሄደ ይገኛል፡፡ ጥናቱ በሶስት ሴክተሮች ማለትም በገቢዎችና ጉምሩክ፣ በፍርድ ቤቶችና በትምህርት ሴክተር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህ ጥናትም በገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ ላይ ያለውን የሙስና ስጋት የሚያሳይ ነው፡፡ ሀገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ለማድረግ የሀገርን ወጪ በሀገር ገቢ መሸፈን የማይተካ ሚና አለው፡፡ በመሆኑም ይህንን አላማ በፍትሀዊነትና በጥራት ለማከናወን ገቢዎችና ጉምሩክ ከሙስና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን መዳሰስ፣ መለየትና አስፈላጊውን የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል፡፡ በገቢዎችና ጉምሩክ አሰራር ውስጥ ያሉ ችግሮችን በትኩረት መለየትና የተሰጠውን ተግባራት በአግባቡ ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ለማከናወን ሙስና ትልቁ ተግዳሮት ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

ሙስና በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በማስከተል ሃገር እንደሃገር በማይቀጥልበት ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል ወይም ተቋማትን የማፍረስ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አደገኛ የሆነ የወንጀል አይነት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሃገራት ይህን የተለዋዋጭነት ባህሪ እያሳየ ያለውን የወንጀል ዓይነት ሊመጥን የሚችል የመከላከያ ስልት በመንደፍ ስራ ላይ ለማዋል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ ጥናትም የተጠቀሰውን ችግር መሰረት በማድረግ የተሰራ ነው፡፡ ጥናቱ በአምስት ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን የሚያጠቃልላቸው የጥናቱ ዳራ (background)፣ አላማዎች፣ ወሰን (scope) እና ፋይዳ፣ የጥናቱ ስነ-ዘዴ፣ የሙስና ስጋት ጥናት ንድፈ-ሀሳባዊ ሞዴል፣ የሙስና ስጋቶች ልየታ፣ ትንተና እና ግምገማ እንዲሁም በመጨረሻ የጥናቱ ማጠቃለያ (summary) ናቸው፡፡

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the Study)

ሙስና የአንድን አገር መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ እድገት እና የሰብአዊ መብት መከበር በከፍተኛ ሁኔታ ከሚጎዱ ችግሮች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ሙስና ማለት ባለስልጣኖች/ሀላፊዎች ከህብረተሰቡ የተሰጣቸውን አደራ ለግል መበልጸጊያ የማዋል ብልሹ አሰራር ማለት ነው፡፡ ሐቀኝነትን የማጉደል ወይም ሕገ-ወጥ ባህሪ ማለት ነው፡፡ ሙስና የህግ የበላይነትን በማጣመም እና ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን ተቋማዊ መሰረት በማቀጨጭ ልማትን ያዳክማል፣ ለማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማነቆ ይሆናል፣ በመሰረተ ልማት፣ በተቋማት እና በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስትመንቶችን በማዳከም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምህዳርን ያጎለብታል፡፡ የሞራል እሴቶች ማሽቆልቆል እንዲሁም ህገ-መንግስታዊ ተቋማትን እና ስልጣንን አለማክበር የሙስና መገለጫዎች ናቸዉ፡፡

ሙስና ኢኮኖሚያዊ፣ ህጋዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ፅንሰ ሃሳብ ወይም በአጭሩ ሁለገብ (ባለ ብዙ ገጽታ) ፅንሰ ሃሳብ በመሆኑ የተነሳ የተለያዩ በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉ ግለሰቦች፣ አለም

አቀፍ የልማት ድርጅቶች እና ሙስና ላይ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለቃሉ የሚሰጡት ትርጓሜ የተለያየ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥም የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ሙስና የመንግስት ስልጣንን ወይም የተሰጠን ሹመት ለግል ጥቅም አላግባብ ማዋል፣ ጉቦ ወይም የማይገባ ጥቅም መቀበል፣ በስልጣን መነገድ፣ በዝምድና እና በወዳጅነት መስራት፣ በምዝበራ አማካኝነት መጠቀም ነው በማለት ቃሉን ይተረጉመዋል፡፡ በአለማችን በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ እና ትግል ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የያዘው መንግስታዊ ያልሆነው ድርጅት ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ደግሞ ሙስና የተሰጠ ስልጣንን ለግል ጥቅም ሲባል አላግባብ መገልገል ማለት እንደሆነ በአጭሩ ያስቀምጣል፡፡ ድርጅቱ በሰጠው ትርጓሜ ውስጥ "የግል ጥቅም" ማለት ከገንዘብ አንስቶ ቁሳቁስ፣ እንዲሁም ከቁሳቁስ ውጪ እንደ የፖለቲካ ወይም የስራ ጥቅም ማግኘት የመሳሰሉትን ያካተተ ነው፡፡ የሙስና አተረጓጉም ቢለያይም ቅሉ አብዛኞቹ ፀሐፍት ሥልጣንን ጠቅልሎ መያዝ፣ ከተጠያቂነት ራስን ነፃ ማድረግ እና ማታለልን/መዋሸትን የሚያካትቱ የሥነ ምግባር ጉድለቶች መሆናቸውን ይስማሙበታል፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል አገሮች፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡ እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና/ወይም የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እና ሀብታቸውን በጣም አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

የፌደራል የስነ-ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ አመታት ህጎችን በማውጣት እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ግን ለሙስና ስጋት የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጀቶችና አሰራሮችን በመለየት ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ ባለመሰራቱ፣ ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አደራጅቶ ወደ ተግባር ቢገባም፣ እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት የተገኘዉ ዉጤት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም፡፡

እንደሚታወቀው ሀገራት የሰው ሀይል፣ የመሰረተ ልማት እና የማህብረተሰብ አገልግሎት አቅርቦትን ፋይናንስ ለማድረግ የሚያስችል ገቢ የሚያገኙበት መሰረታዊ መንገድ ግብር ነው፡፡ በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በህገወጥ ተግባር ለመሰማራት ዕድሎች እና የተመቻቹ

ሁኔታዎች (conducive environment) ብዙ በመሆናቸው የገቢዎች ዘርፍ ለሙስና በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ከሆኑት የመንግስት ሴክተሮች መካከል ይመደባል፡፡ በዘርፉ ባሉ ተቋማት ጉቦ መቀበል (bribery)፣ ገንዘብን (ወይንም ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን) በኃይል/በማስፈራራት ማግኘት (extortion)፣ በአደራ የተሰጠን ገንዘብ/ንብረት መስረቅ ወይም አላግባብ መጠቀም (embezzlement)፣ የገንዘብ ወይም የግል ጥቅምን ለማስገኘት የታሰበ የማታለል ተግባር (fraud) እና የመሳሰሉት የሙስና ዓይነቶች የመከሰት እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ሊከሰቱ ለሚችሉት የሙስና ዓይነቶች የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነ ምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራርብ፣ አያያዝ እና አፈታት ግልጽነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ ደካማነት፣ ወዘተ እንደ ተቋማዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ክስተቶች በገቢዎች ዘርፍ ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ይህን የሙስና ስጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በገቢዎች ዘርፍ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ስጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ በሆነ የሙስና ስጋት የዳሰሳ ጥናት እንዲሁም በተቋማት የጎላ ተሳትፎ እና ውይይት የሙስና መከላከያ ምክረ ሀሳቦችን ለማቅረብ ይህ ጥናት ተዘጋጅቷል፡፡

1.2. የጥናቱ ዓላማዎች (Objectives of the Study)

1.2.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በገቢዎች ዘርፍ ሥር ባሉ ተቋማት (በገቢዎችና ጉምሩክ) ውስጥ የሙስና ስጋት ጥናት በማካሄድ ሙስናን ለመቀነስ ምክረ-ሃሳብ መስጠት ይሆናል፡፡

1.2.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

በገቢዎች ዘርፍ ሥር ባሉ ተቋማት፤

1. የሙስና ስጋቶችን መለየት
2. የተለዩትን የሙስና ስጋቶቸ ምንነት እና መንስዔዎች መተንተን
3. የሙስና ስጋቶች የመከሰት እድል እና ቢከሰቱ ሊያደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ መገምገም
4. በጥናቱ ግኝቶች ላይ በመመርኮዝ በሙስና ስጋት ላይ የመፍትሔ ምክረ-ሃሳቦችን መስጠት፣

1.3. የጥናቱ ፋይዳ (Significane of the Study)

ይህንን ጥናት ስፖንሰር ያደረገው የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እስከሆነ ድረስ ኮሚሽኑ በራሱ መንገድ ለፖሊሲ ግብአት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ በተጨማሪም ከዚህ በኋላ ከሙስና ጋር በተያያዘ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ አንድ ማጣቀሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

1.4. የጥናቱ ወሰን (Scope of the Study)

የዚህ ጥናት ወሰን በአላማ-ተኮር የተመረጡ ከፌዴራል እስከ ዞን ያሉ የገቢዎች ተቋማት እና በጉምሩክ ኮሚሽን ሥር ያሉ የፌዴራል ተቋማት ናቸዉ፡፡ ሁሉንም በገቢዎች እና ጉምሩክ ስር ያሉ ቅርንጫፎችና መስሪያ ቤቶች ማጥናት ቢቻልም ጥናቱ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ትኩረቱ የተመረጡት ቅርንጫፎችና መስሪያ ቤቶች ላይ ብቻ ነው፡፡

1.5. የጥናቱ ውስንነት (Limitations of the Study)

ጥናቱ የተካሄደው በተመረጡ የገቢዎች እና ጉምሩክ ተቋማት ላይ በመሆኑ በዘርፉ ውስጥ ያለውን የሙስና ስጋት አመላካች ከመሆን ባሻገር በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ባሉት የዘርፉ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ያሉትን ክፍተቶች ሙሉ በሙሉ ላያሳይ ይችላል፡፡ በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ውስጥ የነበረው የቋንቋ አለመግባባት ችግርም በተሰበሰበው መረጃ ላይ የራሱ ተፅእኖ አልነበረውም ማለት አይቻልም፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ተቋማት ሰነዶችን (ለምሳሌ የውስጥ/የውጭ ኦዲት ሪፖርቶችን) ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው የተሰበሰበው መረጃ በተወሰነ መልኩ ምሉእ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

ክፍል 2፡- የጥናቱ ስነ-ዘዴ

2.1. የጥናቱ ቦታ (Study Area)

ይህ ጥናት የተካሄደው በፌደራል ደረጃ የተዋቀሩ የገቢዎችና ጉምሩክ መስሪያ ቤቶች፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ በተመረጡ የዘርፉ ተቋማት ላይ ነው፡፡ በተለይ በገቢዎች ንዑስ ዘርፍ ጥናቱ የተካሄደባቸው ቦታዎች፡- በአዲስ አበባ አስተዳደር ሶስት ክፍለ-ከተማዎች (አራዳ፣ ቦሌ እና ንፋስ ስልክ ላፍቶ)፣ በኦሮሚያ ክልል ሶስት ዞኖች (ጅማ፣ ምስራቅ ሸዋ እና ምዕራብ አርሲ) እና በደቡብ ክልል ሶስት ዞኖች (ጋሞ፣ ጉራጌ እና ወላይታ) ናቸው፡፡

የዞን ገቢዎች ተቋማት የክትትል እና ድጋፍ ስራ ብቻ ስለሚሰሩ ለጥናቱ የተሟላ መረጃ ላይሰጡ ይችላሉ በሚል ታሳቢነት መረጃ አሰባሰቡ የወረዳ ገቢዎች ተቋማትንም እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ ለዚህ ተግባር በዞን ዋና ከተሞች ወይም ባቅራቢያ የሚገኙ የወረዳ ገቢዎች ቢሮዎች ተመርጠው መረጃ ተሰብስቧል፡፡

2.2. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design) እና አቀራረብ

ጥናቱ ገላጭ (discriptive) ሲሆን አቀራረቡ ቅይጥ (mixed) የጥናት ዓይነት ነው፡፡ ይህ ዘዴ አሀዛዊ/መጠናዊ (quantitative) እና ዓይነታዊ (qualitative) መረጃዎችን በተመሳሳይ ጥናት ውስጥ መጠቀም ያስችላል፡፡ አቀራረቡ ቅይጥ ቢሆንም የጥናቱ አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ ነው፡፡

2.3. የጥናቱ ተሳታፊዎች (Study participants)

የተሳካ የሙስና ስጋት ግምገማ ስለአንድ ተቋም አሠራር ጥብቅ ዕውቀት ካላቸው ሰዎች ተሳትፎና ግብዓት ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በገቢዎች ዘርፍ ሥር ባሉ ተቋማት የሚገኙ ከፍተኛ የአስተዳደር አባላት እንዲሁም እንደ ታክስ ኦዲት፣ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት፣ የውስጥ ኦዲት፣ ህግ ክፍል፣ ግዥ እና ፋይናንስ፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ ወዘተ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ተካተዋል፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችም ከነዚህ አካላት ተሰብስቧል፡፡ በዘርፉ ስር ያሉት የመረጃ ምንጭ የሥራ ክፍሎች/ቦታዎች እንዲሁም በእያንዳንዱ የሥራ ክፍሎች ዉስጥ የሚገኙት ሂደቶች/ተግባራት ልየታ ተከናውኖ በሠንጠረዥ 1 ውስጥ እንደሚታየው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡- ተቋማት እና የተለዩ የሥራ ክፍሎቻቸው

የገቢዎች ተቋማት የተለዩ የስራ ክፍሎች	የጉሙሩክ ተቋማት የተለዩ የስራ ክፍሎች
• ታክስ ኦዲት ክፍል፣ • ኢንስፔክሽን ኦዲት ክፍል፣ • የታክስ ተመላሽ ስርዓት ክፍል፣ • የታክስ እዳ አስተዳደር ክፍል፣ • የሸያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር ክፍል፣ • ኢንተለጀንስ አስተዳደር ክፍል፣ • የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ስርዓት ክፍል፣ • የንብረት አስተዳደር፣ • የቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር፣ • የህግ አገልግሎት፣ • የውስጥ ኦዲት፣ • የግዥ እና ፋይናንስ፣ • የሰው ሃይል አስተዳደር፣ • የፕላንና ለውጥ ሥራ አመራር፣ • የገቢ አወሳሰን፣ • የገቢ አሰባሰብ፣ • የትምህርት ክትትልና ድጋፍ፣ • ስነምግባር ክፍል፣	• የውስጥ ኦዲት፣ • የጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ፣ • የተቋማዊ ሥጋት ሥራ አመራርና ሥነ-ምግባር መከታተያ፣ • የፕላንና ለውጥ ሥራ አመራር፣ • የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ፣ • የኢንተለጀንስና የኮንትሮባንድ መከላከል፣ • የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት፣ • የህግ አገልግሎት ፣ • የትራንዚትና የመጋዝን አስተዳደር፣ • የወጪና ንግድ ያልሆኑ እቃ አወጣጥ፣ • የገቢ ንግድ ዕቃ አወጣጥ፣ • ኤርፖርት መንገደኞች ጓዝ፣ • የተወረሱ እቃዎች መጋዝን አስተዳደር፣ • የሰው ሃብት ሥራ አመራርና ልማት ፣ • የሀብት አስተዳድር እና የመረጃ ቴክኖሎጂ፣

2.4. **የናሙና ስብጥር** (Distribution of Sample Respondents)

ከላይ እንደተጠቀሰው የጥናቱ ናሙና ከገቢዎች ዘርፍ በዓላማ ተኮር የናሙና መረጣ ስልት (purposive sampling) የተመረጡ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ የተመረጡት መላሾችም ለዚህ ጥናት የተዘጋጀውን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በገቢዎች ዘርፍ ለጥናቱ የተመረጡ ተቋማት እንዲሁም የመጠይቅ እና የቃለ-መጠይቅ ተሳታፊዎች ብዛት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ 2 ተቀምጧል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡- የተመረጡ ተቋማት እና የመጠይቅ/ቃለ-መጠይቅ መላሾች ብዛት

የገቢዎች ተቋማት እና ቅርንጫፎቻቸው		የጉምሩክ ተቋማት	
የገቢዎች የፌደራል ተቋማት (መጠይቅ መላሾች/ቃለመጠይቅ መላሾች)		**የጉምሩክ ተቋማት** (መጠይቅ መላሾች/ቃለመጠይቅ መላሾች)	
የገቢዎች ሚኒስቴር	46/2	የጉምሩክ ዋና ኮሚሽን	34/2
አዲስ አበባ ከፍተኛ ግብር ከፋይ ጽ/ቤት	41/2	ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት	34/2
አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋይ ጽ/ቤት	40/2	ቦሌ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት	34/2
ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት	40/2	ሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት	38/3
የክልል ገቢዎች ተቋማት (መጠይቅ መላሾች/ቃለመጠይቅ መላሾች)		አዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት	34/2
		ድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት	37/2
ኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ቢሮ ጅማ ዞን (ጅማ) ምስራቅ ሸዋ ዞን (አዳማ) ምዕራብ አርሲ ዞን (ሻሸመኔ)	26/2 26/2 26/2 26/2		
ደቡብ ክልል ገቢዎች ቢሮ ጉራጌ ዞን (ወልቂጤ) ጋሞ ዞን (አርባ ምንጭ) ወላይታ ዞን (ሶዶ)	26/2 26/2 26/2 27/2		
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ቦሌ ክ/ከተማ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት የካ ክ/ከተማ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት አራዳ ክ/ከተማ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት	42/2 40/2 40/2 40/2		
ገቢዎች ድምር	**538/32**	**ጉምሩክ ድምር**	**211/13**
ጠቅላላ (ገቢዎች + ጉምሩክ) ድምር		749/45	

2.5 የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች የዳሰሳ መጠይቆች፣ ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ናቸው፡፡ ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ለሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

መጠይቅ፡- የሥራ ክፍል ኃላፊዎችና ሰራተኞች የተዘጋጀውን የዳሰሳ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ለሙስና ስጋት የሆኑ ምክንያቶች እና የት እንደሚፈፀሙ እንዲሁም በየተቋማቱ ሊኖሩ የሚችሉ የሥነ ምግባር ጉድለቶችን የሚያመላክቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ቃለ-መጠይቅ፡- በዚህ ጥናት ከየተቋማቱ በዓላማ-ተኮር ከተመረጡ እና ጠቃሚ ግብአት ሊሰጡ ይችላሉ ተብለዉ ከታመኑ ሠራተኞች ጋር ጥልቅ ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል፡፡ በዚህ ቃለ-መጠይቅ በተቋማቱ ስለሚከሰቱ ብልሹ አሰራሮች፣ የሚፈጸምባቸው ምክንያቶች፣ እና ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች ጥልቅ ውይይት ተደርጓል፡፡

ሰነዶች:- የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ የሽያጭ መጠን ዕቅዶች፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች ተዳሰዋል፡፡

የሀሳብ ማጎልበቻ ዉይይት:- የጥናት ቡድኑ ውስጣዊ እና ውጫዊ መረጃዎችን ፈትሾ ያገኘውን የምርመራ ዉጤት እንደመነሻ ሀሳብ በማቅረብ በጥንቃቄ ከተመረጡ የተቋማት ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ስለ ስጋቶች እና ተጋላጭነቶች እንዲሁም በስራ ላይ ስላሉት የቁጥጥር ዘዴዎች አግባብነት፣ አቅም እና ውጤታማነት ሃሳብ የማጎልበት ውይይት አካሂዷል፡፡ ከውይይቱ የተገኙ በመረጃ የተደገፉ ፍሬ ሀሳቦችን ከሰነዶች፣ መጠይቆች እና ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች ከተገኙ መረጃዎች ጋር አጠናክሮ የሙስና (የብልሹ አሰራር) የመከሰት እድል እና ቢከሰት ሊያደርስ የሚችለውን የጉዳት መጠንም ገምግሟል፡፡

2.6 የጥናቱ የትንተና እና ግምገማ ዘዴ

በዚህ ጥናት ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን ለመተንተን ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች (ቃለ-መጠይቆች፣ ሰነዶች፣ የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች፣ ወዘተ) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያላቸውን እንደ የይዘት ትንተና (content analysis)፣ የትረካ ትንተና (narrative analysis)፣ እና ጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ተጠቅሟል፡፡

ይህ ክፍል መጀመሪያው ያተኮረው ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን መለየት ላይ ነው፡፡ ልየታው ከተከናወነ በኋላ የጥናት ቡድኑ ለሙስና ስጋት መከሰት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ አሰራሮች በምን መልኩ እና የት ተከሰቱ የሚሉትን ጉዳዮች እያንዳንዱን የሙስና ስጋት መሰረት ባደረገ መልኩ ተንትኗል፡፡ በመጨረሻም የስጋቶቹ የመከሰት ዕድል እንዲሁም ቢከሰቱ የሚያስከትሉት ጉዳት ከነመፍትሔያቸው ተመላክተዋል፡፡ ጥናቱ የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድልን እንዲሁም የተጽዕኖን (የጉዳት መጠንን) ለመገምገም የተጠቀመባቸው ሚዛኖች ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ በሚል የደረጃ ክፍፍል ነው፡፡ ይህ ክፍፍል የአለም አቀፍ ስታንዳርድ ሲሆን የደረጃዎቹ መቁረጫ ስኬሎች ውሳኔ መሰረት ያደረገው በመጠይቅ ከተገኘው መረጃ ትንተና ውጤት፣ ከቃለ-መጠይቅና የሰነድ መረጃ ትንተና ውጤት እንዲሁም ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሙያዎች ጋር በተደረገ ሀሳብ ማጎልበቻ ውይይት (brainstorming) ነው፡፡ ለዚህ ተግባር ጥናቱ የተጠቀመበት የዳሰሳ መጠይቅ መረጃ ትንተና በዚህ ሪፖርት መጨረሻ ላይ በአባሪነት ተያይዟል፡፡

ሰንጠረዥ 3፡ የሙስና ስጋቶችን መገምገሚያ ሚዛኖች

የመከሰት ዕድል	መግለጫ
ዝቅተኛ	በመጠይቁ ትንተና ውጤት መሰረት ከ 25% በታች መላሾች የመከሰት ዕድልን ከተስማሙበት፣ በተጨማሪም ከሁሉም የጥናት ተቋማት እና ቅርንጫፎቻቸው የተገኙ የቃለ-መጠይቅ፣ የዶኩመንት ማስረጃዎች እና ሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) የመከሰት እድል ዝቅተኛ መሆኑን ሲደግፉት
መካከለኛ	በመጠይቁ ትንተና ወጤት መሰረት ከ 25% እስከ 50% መላሾች የመከሰት ዕድልን ከተስማሙበት፣ በተጨማሪም ከሁሉም የጥናት ተቋማት እና ቅርንጫፎቻቸው የተገኙ የቃለ-መጠይቅ፣ የዶኩመንት ማስረጃዎች እና ሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች ሙስናው በመካከለኛ ደረጃ ሊከሰት እንደሚችል ሲያመላክቱ
ከፍተኛ	በመጠይቁ ትንተና ወጤት መሰረት ከ 50% በላይ መላሾች የመከሰት ዕድልን ከተስማሙበት፣ በተጨማሪም ከሁሉም የጥናት ተቋማት እና ቅርንጫፎቻቸው የተገኙ የቃለ-መጠይቅ፣ የዶኩመንት ማስረጃዎች እና ሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች ሙስናው በከፍተኛ ደረጃ ሊከሰት እንደሚችል ሲያመላክቱ
የተጽዕኖ መጠን	**መግለጫ**
ዝቅተኛ	ከሀሳብ ማጎልበቻ ውይይት፣ ከዶኩመንት እና ከቃለ-መጠይቅ ባገኘነው መረጃ መሰረት ሙስናው ከተከሰተ የሥራ ሂደቶች እና የታቀዱ ተግባራት ቀላል ተጽዕኖ ብቻ ያጋጥማቸዋል፣ የንብረት/ገንዘብ ኪሳራውም አነስተኛ ነው (loss of minor assets) የሚል መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ በዚህ ደረጃ የለየናቸው የሙስና ስጋት አይነቶች ተጽዕኖ ዝቅተኛ በሚል ተወስኗል፡፡
መካከለኛ	ከሀሳብ ማጎልበቻ ውይይት፣ ከዶኩመንት እና ከቃለ-መጠይቅ ባገኘነው መረጃ መሰረት ሙስናው ከተከሰተ የስራ እንቅስቃሴዎች እና የታለሙ ግቦች በከፍተኛ ሁኔታ ይስተጓጎላሉ የሚል መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ በዚህ ደረጃ የለየናቸው የሙስና ሰጋት አይነቶች ተጽዕኖ መካከለኛ በሚል ተወስኗል፡፡
ከፍተኛ	ከሀሳብ ማጎልበቻ ውይይት፣ ከዶኩመንት እና ከቃለ-መጠይቅ ባገኘነው መረጃ መሰረት የሥራ ሂደቶች እና የታቀዱ ተግባራት ሙሉ ለሙሉ ይስተጓጎላሉ (ምሳሌዎች፡- የሁሉም አስፈላጊ አገልግሎቶች መቋረጥ፣ የዋና ዋና ንብረቶች ወይም ከፍተኛ የገንዘብ ኪሳራ (loss of major assets) በሀገሪቷ ላይ ያደርሳል) የሚል መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ በዚህ ደረጃ የለየናቸው የሙስና ሰጋት አይነቶች ተጽዕኖ ከፍተኛ በሚል ተወስኗል፡፡

ክፍል 3:- የሙሰና ስጋት ጥናት የንድፈ ሃሳባዊ ሞዴል

ይህ የንድፈ ሃሳባዊ ሞዴል አምስት ደረጃዎች አሉት። እያንዳንዱ ደረጃ በቅደም ተከተል ምን መሰራት እንዳለበት እንዲሁም እንዴት መሰራት እንዳለበት በዝርዝር ያስቀምጣል። ይህንን መሰረት በማድረግ ተግባራዊ የሆነ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ይቻላል። እያንዳንዱ ደረጃ እና ትንታኔው ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ተብራርቷል።

3.1. ስለጥናቱ አጠቃላይ ግንዛቤ ማሳደግ እና ተሳታፊዎችን መለየት (1ኛ)

የጥናት እና የመስክ (field) ቡድን አባሎች ጥናቱ በሚካሄድባቸው ተቋማት ለሚገኙ ሰራተኞች የሙስና ስጋት ጥናት አላማ እና አስፈላጊነት በሚገባ ያስተዋውቃሉ። የሙስና ስጋት ትንተና “ሌቦችን” ወይም “ሙሰኞችን” የሚያስስ ሳይሆን ውጤታማ የሙስና መከላከያ መሳሪያ መሆኑን እንዲሁም የተቋሙን ታማኝነት፣ መልካም ስምና ዜጎች የሚያሳድሩበትን እምነት እንዲጨምር የሚረዳ መሆኑን ግንዛቤ መስጠት ያስፈልጋል። ይህንን መሰረት በማድረግ የጥናት ቡድኑ የሙስና አደጋዎችን ለመለየት የሚያስችሉትን የተለያዩ የመረጃ ምንጮች (ሃሳብ የማጎልበት ውይይት (brainstorming)፣ መጠይቆች፣ ቃለ-መጠይቆች፣ ሰነዶች፣ የጥናት ሥነ-ጽሑፎች (literature reviews) ልየታ ያደርጋል።

3.2. የተቋሙን የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት መለየት (2ኛ)

የዚህ እርምጃ አላማ በዘርፉ ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ የሙስና እንዲሁም የሌሎች ህገ-ወጥ እና ኢ-ስነ-ምግባሮች ሥጋቶችን መለየት ነው (የት ፣ መቼ ፣ ለምን እና እንዴት ሊከሰቱ እንደሚችሉ)። የእዚህ ልየታ ትኩረቱ ዘርፉ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ሰለባ ሊሆን የሚችልባቸውን ሁሉንም አይነት የሙስና ሥጋቶች መዘርዘር ሳይሆን ይልቁንም ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተጨባጭ እና መስተካከል የሚችሉ ስጋቶችን ዝርዝር ማውጣት ነው። በሌላ አገላለጽ በአንድ የተወሰነ ተቋም ውስጥ በተለመደው አሠራር ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ተጨባጭ የሙስና ዓይነቶች ላይ ብቻ ማተኮር ያስፈልጋል።

በመጀመሪያ የጥናት ቡድኑ ድክመቶችን እና የሙስና አደጋዎችን ለመለየት የሚረዱትን ከተቋሙ ጋር የተያያዙ ውስጣዊ እና ውጫዊ መረጃዎች ይመረምራል። ለዚህ ተግባር ከሚረዱ የመረጃ ምንጮች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፦ የውስጥ ቁጥጥር (internal controls) ሪፖርቶች፣ የውስጥ እና የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች፣ የዜጎች ቅሬታዎች፣ የጠቋሚዎች መረጃ (whistleblowers' information) እና ከዚህ በፊት ያጋጠሙ የሙስና ጉዳዮች ሪፖርቶች፣ ግልጽ ያልሆኑ የህግ ማዕቀፎች፣ የውስጥ ደንቦች እና ሂደቶች፣ ያልተጣጣሙ (inconsistent) የመተዳደሪያ ደንቦች፣ ለተመሳሳይ ጉዳይ የወጡ የተለያዩ ደንቦች (እነዚህ ክፍተቶች ለከፍተኛ ግላዊ ስልጣን (discretionary powers) ያጋልጣሉ)፣ የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች፣ የህዝብ አስተያየቶች፣ የዳሰሳ ጥናቶች፣ የሥራ አካባቢ ውስጣዊ ቅኝቶች።

በመቀጠልም የምርመራ ዉጤቱ ላይ በመመርኮዝ የጥናት ቡድኑ በእያንዳንዱ የስራ ሂደት ውስጥ ያሉትን ስጋቶች እና ተጋላጭነቶች የመለየት ተግባር ያከናዉናል። ይህን ለማከናወን የሚከተሉት ሶስት አማራጮች/መንገዶች በጣም የተለመዱ ናቸው፡-

1. ከተቋሙ ሃላፊዎች እና ሰራተኞች ጋር ስለ ሥጋቶች እና ተጋላጭነቶች ሃሳብ የማንሸራሸሪያ ሥራ (brainstorming) ማካሄድ፣
2. አስቀድመው የተዘጋጁ አመላካቾችን (indicators) በመጠቀም መለየት፣
3. የሁለቱ መንገዶች ጥምረት፣

የተሻለ የሚሆነው 3ኛውን አማራጭ መጠቀም ነው። የጥናት ቡድኑ ውስጣዊ እና ውጫዊ መረጃዎን ፈትሾ ያገኘውን የምርመራ ዉጤት እንደመነሻ ሀሳብ በማቅረብ በጥንቃቄ ከተመረጡ የተቋሙ ሃላፊዎች እና ሰራተኞች ጋር ስለ ሥጋቶች እና ተጋላጭነቶች ሃሳብ የማንሸራሸሪያ ሥራ ያካሂዳል። ይህ ጥናት የዘርፎቹን የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ለመቀነስ ታስቦ የሚሰራ እንጂ ምርመራ እንዳልሆነ ለተቋሙ ሰራተኞች አፅንዖት መስጠት አስፈላጊ ነው - ታዓማኒ መረጃን ለማመንጨት ስለሚያስችል። በመቀጠልም ምንም ዓይነት ተጠያቂነት እንደማያመጣ ለጥናቱ ተሳታፊዎች በማረጋገጥ ለተቋሙ የተዘጋጀዉን የጥናት መጠይቅ በነፃነት እንዲሞሉ ያደርጋል።

3.3 የተቋሙን የሙስና ስጋቶች መተንተን (3ኛ)

የሙስና ስጋቶች ትንተና በደረጃ ሁለት በዝርዝር ተለይተው የታወቁትን አደጋዎች ተፈጥሮ (nature) እና መንስኤ (drivers) ለመረዳት፣ እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ ያሉትን መቆጣጠሪያዎች (controls) ውጤታማነት ለመመርመር የሚያገለግል ሂደት ነው።

ለሙስና መከሰት መንስዔዎች ውስጣዊ፣ ውጫዊ፣ የአሠራር (operational) እና የግለሰብ ተጋላጭነቶች ናቸው። በዚህ ደረጃ ላይ እያንዳንዱ የሙስና ስጋት ለምን ሊከሰት እንደቻለ ውይይት መደረግ አለበት። መረጃው በቀላሉ በሚገኝበት ጊዜ በሙስና ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ያልተለመዱ ሁኔታዎችን (unusual patterns) ለመለየት ተዛማጅ መዝገቦችን መመርመር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። እንደዚህ አይነት መረጃዎች በቀላሉ የማይገኙ ከሆነ የሙስና ስጋት ቅነሳ (mitigation) እቅዱ ወደፊት መረጃዎች ተጠናክረው መቀመጥ እንዳለባቸው ድንጋጌዎችን ማካተት አለበት።

በዚህ ደረጃ ከሚከናወኑ ተግባራት አንዱ የነባር (current) ሙስና መቆጣጠርያዎች ዳሰሳ ይሆናል። ይህም አሁን በተግባር ላይ ያሉትን መቆጣጠሪያዎች አግባብነት፣ አቅም እና ውጤታማነት ለመገምገም ይረዳል። ለምሳሌ የተቀረፁ መቆጣጠሪያዎች ሙስናን ለመከላከል አለመቻላቸውን ወይም ያሉትን የሙስና መቆጣጠሪያዎች በተደጋጋሚ የመሻር/ወደጎን የመተው (override) ክስተቶች መኖራቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ከተገኘ የሙስና ስጋት እንዳለ፣ አሁን

ያሉት የሙስና መቆጣጠሪያዎች ችግር እንዳለባቸው እና እንደገና መፈተሽ እንደሚገባቸው የሚያሳዩ ጠንካራ ምልክቶች ናቸው።

በዚህ ትንተና ውጤት መሰረት የጥናት ቡድኑ እያንዳንዱን የሙስና ስጋት በሚከተሉት መደቦች ይከፋፍላል፦

- የቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋለት (መቆጣጠርያዎች (controls) ተገቢ እና በቂ ናቸው)፣
- ከፊል የቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋለት (መቆጣጠርያዎችን ማዘመን እና ማሟላት ያስፈልጋል)፣ ወይም
- የቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋለት (መቆጣጠርያዎች የሉም ወይም በቂ አይደሉም)።

የሙስና ስጋቱን በዚህ መንገድ መመደብ በተለይ ስለ ተጽእኖው (impact) ለሚደረገው ግምገማ ጠቃሚ ይሆናል።

3.4 የተቋሙን የሙስና ስጋቶች መገምገም (4ኛ)

አንድ ተቋም ሊያጋጥሙት ይችላሉ ተብለው ለሚታሰቡት ለእያንዳንዱ የሙስና ስጋቶች የመፍትሄ እርምጃ ማጠናከር እጅግ አስቸጋሪ ሲሆን ተግባራዊ የመሆን ዕድሉም ዝቅተኛ ነው። በመሆኑም በዚህ ደረጃ የጥናት ቡድኑ የትኞቹ የሙስና ስጋቶች ቅድሚያ እንደሚሰጣቸዉ በመገምገም መለየት ይኖርበታል።

በተጨባጭ ሊፈፀሙ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች ዝርዝር ከተዘጋጀ በኋላ ለእያንዳንዱ የሙስና ስጋት ሁለት የተለያዩ ግምቶች ይዘጋጃሉ። እነሱም የአደጋው የመከሰት እድል እና አደጋዉ ቢከሰት ሊያደርስ የሚችለው የጉዳት መጠን ናቸዉ። ሁለቱን ግምቶች በመረጃ በተደገፈ የተቋሙ ሰራተኞች እና የጥናት ቡድን አባላት ግላዊ ዕይታ በመጠቀም በሦስት ደረጃዎች (ዝቅተኛ፣ መካከለኛ ወይም ከፍተኛ) ማስቀመጥ ይቻላል። እንደዚህ ያሉ መለኪያዎች የተለያዩ የሙስና ዓይነቶችን የቅደም ተከተል ትኩረት ለመስጠት ብዙዉን ጊዜ በቂ ናቸው።

እነዚህ ሁለቱ ግምቶች ተዋህደዉ አንድ መለኪያ ይሰጡናል። ይሄ መለኪያ የትኛዉ የሙስና ስጋት ቢከሰት ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ያሳየናል። እነዚህን ግምቶች ለማዋሀድ ቀጥተኛዉ መንገድ ሦስት-በ-ሦስት የሆነ የስጋት ማትሪክስ (risk matrix) ማበጀት ይሆናል። የማትሪክሱ ረድፎች የስጋቱን የመከሰት ዕድል የሚያሳዩ ሲሆን ዓምዶቹ ደግሞ ስጋቱ ቢከሰት ሊያደርስ የሚችለውን የጉዳት መጠን ያሳያሉ (ምስል 1ን ይመልከቱ)።

ምስል 1፡- የሙስና ስጋት ደረጃን መገምገሚያ ማትሪክስ

የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል	**ከፍተኛ**	መካከለኛ	ከፍተኛ	ከፍተኛ
	መካከለኛ	አነስተኛ	መካከለኛ	ከፍተኛ
	ዝቅተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	መካከለኛ
		ዝቅተኛ (አነስተኛ)	**መካከለኛ (መጠነኛ)**	**ከፍተኛ (ከባድ)**
		የተጽዕኖ ደረጃ		

የስጋት ማትሪክሱ ትንተና እንደሚከተለው ይሆናል፦ የመከሰት እድሉ እና ተጽእኖው ሁለቱም "ከፍተኛ" ከሆኑ ወይም አንዱ "ከፍተኛ" ሌላኛው "መካከለኛ" ከሆነ የስጋቱ ደረጃ ከፍተኛ (ከባድ) ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱም ግምቶች "ዝቅተኛ" ላይ ካረፉ ወይም አንዱ "ዝቅተኛ" እና ሌላኛው "መካከለኛ" ከሆነ የስጋቱ ደረጃ እንደ አነስተኛ ይቆጠራል፡፡ በሁለቱ መካከል የሚወድቁት መካከለኛ የስጋት ደረጃ ላይ ይመደባሉ፡፡

ይህንን ትንተና በማድረግ የጥናት ቡድኑ በቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡትን የሙስና ስጋቶች ይለያል፡፡

3.5 የሙስና አደጋዎችን ለማከም የመፍትሔ ሀሳብ ማዘጋጀት (5ኛ)

በዚህ ደረጃ ዉስጥ የጥናት ቡድኑ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸውን የሙስና አደጋዎች ለመከላከል ተቋሙ ሊተገብራቸው የሚገቡ መቆጣጠርያዎችን (controls) ይነድፋል፡፡ መቆጣጠርያዎች ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶችን (improper actions) ለመከላከል የተቀረጹ ፖሊሲዎች፣ ሂደቶች እና የአስተዳደር ስርዓቶች ናቸው፡፡

የመፍትሔ ሀሳብ ዕቅድ በማዘጋጀት ሂደት ዉስጥ የሚከናወኑ ተግባራት፡-

- ✓ ያሉትን መቆጣጠሪያዎች መገምገም፦ የትኛዎቹ መቆጣጠሪያዎች መፈተሽ እንዳለባቸው ለማወቅ የጥናት ቡድኑ የሙስና ስጋቶችን መንስኤ ይለያል፡፡ ቀጥሎም በስራ ላይ ያሉት መቆጣጠሪያዎች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ይገመግማል፡፡
- ✓ የተጨማሪ መቆጣጠሪያዎችን አስፈላጊነት መወሰን፦ ያሉት መቆጣጠሪያዎች በመጠኑ ውጤታማ ከሆኑ ወይም ውጤታማ ካልሆኑ፣ የጥናት ቡድኑ ተጨማሪ መቆጣጠሪያዎችን ይነድፋል፡፡
- ✓ የተጨማሪ መቆጣጠሪያዎችን አዋጭነት (feasibility) መገምገም፦ ተጨማሪ መቆጣጠሪያዎች አንድ የተወሰነ የሙስና አደጋ ሊፈጥር ከሚችለው ጉዳት የበለጠ ዋጋ ሊያስከፍሉ አይገባም፡፡

እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ብዙ ጊዜ የሙስና አደጋዎችን ለመከላከል በቂ መቆጣጠሪያዎች ሲኖሩ የሙስና ስጋቶች ተቀርፈዋል የሚል ግምት አለ፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የሙስና ተግባራት የሚከናወኑት ሰዎች ነባሩን አሠራር ችላ ሲሉና ያሉትን ሕጎች ሲጥሱ ስለሆነ መቆጣጠሪያዎች መዘርጋታቸው ብቻ ሙስናን ለመዋጋትም ሆነ ለማቃለል ዋስትና አይሆንም፡፡

ክፍል 4፡- የሙስና ስጋት ልየታ፣ ትንተና እና ግምገማ

በዚህ ጥናት ውስጥ የገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ ሁለት እራሳቸውን የቻሉ የገቢዎች ክንፍ እና የጉምሩክ ክንፍ አሉት። በጉምሩክ ክንፍ ውስጥ ያሉ ተቋማት ሙሉ በሙሉ በፌደራል ጉምሩክ ኮሚሽን ስር ሲሆኑ፣ የገቢዎች ተቋማት ግን የፌደራል እና የክልል አወቃቀር/አደረጃጀት አላቸው።

ሁለቱ ንዑስ-ዘርፎች የጋራ የገቢ መሰብሰብ ተልዕኮ ቢኖራቸውም የተለያየ የስራ ድርሻ እና አሰራር አላቸው። የገቢዎች ተቋማት ሥልጣንና ተግባር ሁሉንም የሀገር ውስጥ የገቢ ታክሶችን እና ክፍያዎችን መገምገም እና መሰብሰብ ሲሆን፣ የጉምሩክ ተቋማት ዋነኛ የስራ ተግባር ደግሞ ወደ አገር በሚገቡና ወደ ውጭ አገር በሚላኩ ዕቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ ነው። የገቢ ታክስ ክፍያ አብዛኛውን ጊዜ የንግድ ሥራው ከተከናወነ በኋላ የሚደረግ ሲሆን፣ በአንፃሩ አጠቃላይ የጉምሩክ ሂደት (ዲክላራሲዮን ከማስገባት ጀምሮ እስከ ጭነቱ መለቀቅ ድረስ) ጭነቱ ገቢን ከማስገኘቱ አስቀድሞ የሚከናወን ግብይት ነው። በተጨማሪም የገቢ ታክስ ክፍያዎች ሙሉ በሙሉ በሰነዶች ምርመራ ላይ የተመሰረቱ ሲሆኑ፣ የጉምሩክ የገቢ አሰባሰብ ተግባር ግን ከሰነዶች በተጨማሪ የሸቀጦች እና የቁሳቁሶች ምርመራን (ፍተሻን) እና እንቅስቃሴን (movement) መሰረት ያደረገ ነው። እነዚህ ልዩነቶች በእያንዳንዱ ንዑስ-ዘርፍ ውስጥ ያሉት የሙስና ተግባራት ተፈጥሮ እና መጠን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

ከላይ የተገለፁትን መሰረት በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ በገቢዎች እና ጉምሩክ ዘርፍ ውስጥ እየታዩ ያሉ የሙስና ስጋቶች እና ለስጋቶቹ መከሰት መንስዔዎች ተለይተው፣ ተተንትነው እና ተገምግመው ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል። የሙስና ስጋቶቹን ለመቀነስ ያስችላሉ ያልናቸው የመፍትሔ ሀሳቦችም ተቀምጠዋል። አንዳንዶቹ የሙስና ስጋት አይነቶች በገቢዎች እና በጉምሩክ ንዑስ-ዘርፎች ስለሚለያዩ እንደየባህሪያቸው በተናጥል ተተንትነዋል።

4.1. የሙስና ስጋቶች በጉምሩክ ንዑስ-ዘርፍ

1. የዋጋ አተማመን መመሪያን መሰረት ያላደረገ ዋጋ መወሰን

ማብራሪያ፦ ይህ ስጋት የአስመጪዎች እና የአምራቾች ገቢ ዕቃ የግብይት ዋጋው በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዴታ ቤዝ (ECVS) ውስጥ ከአለው ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ በቅደም ተከተል ከ5 በመቶ እና ከ10 በመቶ በላይ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢዎች ላቀረቡት የግብይት ዋጋ ልዩነት ማስረጃ ሳያቀርቡ ቀረጥ እና ታክስ በጉምሩክ የዋጋ መረጃ መሰረት መሰራት ሲኖርበት በቀረበው ኢንቮይስ ዋጋ መስራትን ይመለከታል።

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 158/2011 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2/መ፣ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበ እያንዳንዱ የዕቃ ዋጋ በኩምሩክ የዋጋ መረጃ ዴታ ቤዝ (ECVS) ውስጥ ከሚገኙ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች አማካኝ ዋጋ

ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ በማነስ የንግድ እቃዎች አስመጪ ከ5% በላይ እንዲሁም አምራች ድርጅቶች ከ10% በላይ ከሆነ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ዋጋ ተቀባይነት እንደማይኖረው ይደነግጋል። ሆኖም ግን አቅራቢው በዓለማቀፍ ደረጃ የታወቀ የዋጋ ለውጥ መኖሩን በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ለኮሚሽኑ ማቅረብና ማስረዳት ከቻለ እና በስራ አስኪያጅ ተቀባይነት ካገኘ የንፅፅር ዋጋው ተሽሮ በኢንቮይስ ሊሰራ ይችላል። ሌላው ደግሞ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 158/2011 አንቀጽ 19ን መሰረት በማድረግ በመነሻ (minimum) ዋጋ ቀረጥ እና ታክሳቸው የሚሰላላቸው ዕቃዎች አሉ። እነዚህ ዋጋዎች በየጊዜው የዋጋ ተለዋዋጭነት እየታየ በኮሚሽኑ ማሻሻያ የሚደረግባቸው ናቸው። በዚህ አሰራር መሰረት ከደንበኞች የቀረበው ኢንቮይስ ከመነሻ ዋጋ የበለጠ ከሆነ ተቀባይነት ያገኛል፣ ከዛ በታች ከሆነ ግን ኮሚሽኑ ባስቀመጠው መነሻ ዋጋ መሰረት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ይሰላል። እነዚህን መመሪያዎች ቸል በማለት በዲክላራሲዮን አቅራቢው ኢንቮይስ ዋጋ መስራት የተሳሳተ ተግባር ነው። እንዲህ አይነቱ የተሳሳተ/ብልሹ አሰራር መንግሥት ከቀረጥ እና ታክስ ማግኘት የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል። በተጨማሪም ያለ ማስረጃ የቀረቡት የኢንቮይስ ዋጋዎች ECVS ላይ ለመረጃነት (Reference) ገብተው ሀገር አቀፍ የገቢ ዕቃ ዋጋ መረጃን ሊያፋልሱ ይችላል።

ከዋጋ አወሳሰን ጋር በተገናኘ ለሚከሰቱ ብልሹ አሰራሮች እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉት፦ የመነሻ ዋጋ ያልተቀመጠላቸው በርካታ ዕቃዎች መኖር (በመነሻ ዋጋ የሚስተናገዱ ዕቃዎች በየወቅቱ እየጨመሩ መምጣታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ)፣ በስራ መብዛት ምክንያት የክትትልና የቁጥጥር መላላት ወይም ማነስ፣ ዋጋ አወሳሰን ላይ የሚሰሩ በቂ ባለሞያዎች አለመኖር እንዲሁም ያሉትም ላይ አቅም/ልምድ/ክህሎት ማነስ ናቸው። በተጨማሪም የስነ-ምግባር ጉድለት (ሆን ተብሎ አግባብ ያልሆነ ጥቅም ፍለጋ ለማግኘት)፣ እርምጃ የሚወስድ አካል ኮሚትመንት ማነስ እና ቅጣቱን ለማቅለል በቀረቤታ መወሰን፣ እንዲሁም ጥፋቱና በአጥፊዎች ላይ የሚወሰደው የዲሲፕሊን እርምጃ የተመጣጠኑ አለመሆኑ ሪስክ ለመውሰድ ገፊ መሆኑ በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። እንዲሁም ደረቅ ወደቦችን የሚያስተዳድረው የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት (ባትሎአድ) የሚዛን ፋሲሊቲ የሌለው መሆኑና ቀረጥና ታክሳቸው በክብደት ላይ ተመስርቶ ለሚሰሩ ዕቃዎች (ለምሳሌ ብረታ ብረት) አስመጪው ከጉምሩክ ሰራተኛ ጋር ምድር ሚዛን ያላቸው ድርጅቶች ጋር እየወሰደ ሲያስመዝን የመሞዳሞድ አጋጣሚ መፈጠር እንደ መንኤነት ተጠቃሽ ናቸው።

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ በ16ቱም የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በየቀኑ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የዕቃዎች ዋጋ ተተምኖ ሲስተም ውስጥ ይገባል - በዚህ ሂደት ውስጥ የተሳሳቱ አተማመኖች የመከሰት እድል ከፍተኛ ነው። ጉምሩክ ኮሚሽን በ2013 እና በ2014 በጀት ዓመት የተስተዋሉ ዋና ዋና የስነ-ምግባር ክፍተቶች ብሎ ያወጣቸው ሪፖርቶችም ይህንኑ ያመላክታሉ። ከተለያዩ ሰነዶች እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ኤክስፐርቶች ጋር ካደረግነው ሀሳብ የማጎልበት ውይይት (brainstorming) ባገኘነው መረጃ መሰረት ይህ አደጋ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል (መንግስትን ከፍተኛ ገቢ ያሳጣዋል፣ ሌሎች ሰራተኞች ወደ ሙስና እንዲገቡ ይገፋቸዋል፣ ይህም

ስርአቱ/ሲስተሙ ኮላፕስ እስከማድረግ የሚያደርስ ጉዳት ሊያመጣ ይችላል)፡፡ ስለዚህ የስጋቱ ደረጃ ከፍተኛ ነው፡፡

የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሽፋንን ማሳደግ እንዲሁም ወቅታዊ እና ተደራሽ ማድረግ፣ የቅርብ ሀላፊ ክትትልን ማጠናከር እና አደጋው ከመከሰቱ በፊት ሪስክን መሰረት ያደረገ የመከላከል ስራ መስራት፣ አቅምና ክህሎትን ለማሳደግ መደበኛ የስልጠና ስርአት መዘርጋት፣ አመለካከትን ለመቀየር የተጠናከረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት፣ ለባለሙያዎች ተገቢ ጥቅም (ኢንሴንቲቭ) መስጠት፣ ዋጋ አሳንሶ ጥቅም ለማግኘት ሆን ብለው የሚያደርጉን ሰራተኞች ተጠያቂ ማድረግ እንዲሁም ተመጣጣኝ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ፣ ባትሎአድ ዲጂታል የሆነ ተአማኒ የምድር ሚዛን በየደረቅ ወደብ እንዲተክል ማድረግ፣ አስመጪው ከጉምሩክ ሰራተኛ ጋር ምድር ሚዛን ያላቸው ድርጅቶች ጋር እየወሰደ ሲያስመዝን ሙስና እንዳይሰራ የቁጥጥር ስርአት መዘርጋት (ቼክ ኤንድ ባላንስ) ወሳኝ የማሻሻያ እርምጃዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የዋጋ ትመና ዘዴው ከሪፈረንስ ዋጋ ወደ መነሻ ዋጋ ቢያመዝን የዋጋ አተማመን ፍትሀዊነትን ከማረጋገጥም አልፎ ከስነ-ምግባር ችግር ጋር በተያያዘ የሚነሳ ሀሜትንም ያስወግዳል፡፡ በእርግጥ ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች እጅግ በጣም ብዙ በመሆናቸው ለሁሉም ዕቃዎች የመነሻ ዋጋ መስራት አስቸጋሪ መሆኑ ባያጠያይቅም፤ ቢያንስ ተደጋጋሚ ችግር የሚገኝባቸውን ዕቃዎች በመለየት የመነሻ ዋጋ መትከል ስጋቱን ይቀንሰዋል፡፡

2. *ዕቃዎችን የታሪፍ አጣጣል መመሪያን ያላማከለ ታሪፍ ላይ መመደብ*

ማብራሪያ፦ ይህ ስጋት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ገቢ እቃዎችን ትክክለኛ የብዛት፣ የክብደት፣ የአይነትና የስሪት አገር መረጃዎችን በአግባቡ ሳይጠቀሙ ቀረጥና ታክስ መስራትን/ገቢ ዕቃዎችን በተሳሳተ የሀርሞናይዝድ ሲስተም ቁጥር መዝግቦ ገቢ ማድረግን ይመለከታል፡፡

ይህ ብልሹ አሰራር በታሪፍ አመዳደብ እና ትክክለኛውን ቀረጥና ታክስ ከማስከፈል አንፃር የመንግሥት ገቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፣ በተጨማሪም የተጋነነ ታሪፍ በመወሰን ባለጉዳዩን አስደንግጦ ለድርድር በማቅረብ ህገ-ወጥነት እንዲስፋፋና ሌብነት ስር እንዲሰድ በር ይከፍታል፡፡ ለችግሩ መከሰት እንደ ዋነኛ ምክንያትነት የተነሱት የታሪፎች በየጊዜው መቀያየር፣ በገንዘብ ሚኒስቴርና በጉምሩክ ኮሚሽን መካከል የቅንጅት ክፍተት መኖር (የታሪፍ ማሻሻያዎች በገንዘብ ሚኒስቴር ከወጡ በኋላ በጉምሩክ ሲስተም (ECMS) *ውስጥ ገብተው ተግባራዊ እስከሚደረጉ ድረስ የቀናት ልዩነት መኖር)፣ እንዲሁም ከሥራው ብዛት አኳያ በአንድ ቡድን ሥር የተደለደለው የሰው ሀይል በጣም ብዙ በመሆኑ እያንዳንዱን ጉዳይ በቅርበት ለመከታተልና ለመቆጣጠር እጅግ ከባድ መሆኑ ናቸው፡፡ የሰው ሀይልን በተመለከተ የማትጊያና ማቆያ ስርዓት ባለመኖሩ ልምድ ያላቸው (ሲኒየር) ኦፊሰርስ ከስራ መልቀቅ፣ በቂ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል የማግኘት ችግር እንዲሁም አዲሶቹ ደግሞ በቶሎ አዳፕት ማድረግ መቸገራቸው (አቅም እና ልምድ ማነስ) እንደ እንቅፋትነት ተነስተዋል፡፡ የስነ-ምግባር ችግርም (ሆን ብሎ በዝቅተኛ የታሪፍ መደብ መመደብ - በተለይ ከጨርቃ ጨርቅ ጋር በተገናኘ) በዚህ ረገድ የራሱ አስተዋፅኦ አለው፡፡*

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ በ16ቱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ዕቃዎች ታሪፍ ተተምኖ ሲስተም ውስጥ ይገባል፣ ከሥራው ብዛት አኳያ እያንዳንዱን ጉዳይ በቅርበት ለመከታተልና ለመቆጣጠር እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ዕቃዎች በተሳሳቱ የታሪፍ መደቦች ውስጥ የመመዝገባቸው እድል ከፍተኛ ነው፡፡ ወደ 50% የሚጠጉ የቃለ-መጠይቅ መላሾች ከፍተኛ የታክስ/የቀረጥ ዋጋ ያላቸውን እቃዎች በዝቅተኛ ምድቦች የመተመን ስራ እንደሚሰራ ስምምነታቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ችግሩ ስር የሰደደ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ ሰነዶች እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ኤክስፐርቶች ጋር ካደረግነው ሃሳብ የማኅልበት ውይይት ባገኘነው መረጃ መሰረት ይህ ስጋት ከተከሰተ መንግስትን በየቀኑ ብዙ ሚሊዮኖች ያሳጣል፡፡ ከዚህ በመነሳት ይህ ስጋት የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ስለዚህ የስጋቱ ደረጃ ከፍተኛ ነው፡፡

ችግሩን ለመቅረፍ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፦ በገንዘብ ሚኒስቴርና በጉምሩክ ኮሚሽን መካከል ያለውን ቅንጅት በማጠናከር የታሪፍ ማሻሻያዎችን በወቅቱ (ሳይዘገይ) ተግባራዊ ማድረግ፣ የማትጊያና ማቆያ ስርዓት መዘርጋት (አቅም በፈቀደ መጠን)፣ የባለሙያዎችን የሙያ ክህሎት በመደበኛ እና ወቅታዊ ስልጠና ማሳደግ (ከተጠያቂነት ለመሸሽ ሥልጠና አላገኘሁም፣ የእውቀት ክፍተት ነው፣ ወዘተ የሚሉትን ማምለጫዎች ለማስቀረት)፣ በየዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በልዩ ፓኬጅ (ኢንሴንቲቭ) ቀጥሮ በቦታው ላይ መመደብ፣ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር (የተጠናከረ የኦዲት ስርአት መዘርጋት)፣ አጥፊዎችን ተከታትሎ ወደ ሕግ የማቅረብ ስርአትን ማጠናከር (የሚወሰደውን እርምጃም ጠበቅ (የማያዳግምና አስተማሪ) ማድረግ)፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ወደ 80% የሚጠጉ የመጠይቅ መላሾች ሰራተኞች ለረጅም ጊዜ ተጋላጭ ቦታዎችን እንዳይዙ የሰራተኞች ቦታ ዝውውር በተቋማቸው ላይ ተግባራዊ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ ይህ አሰራር ሙስናን ለመከላከል የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የሚካድ ባይሆንም፣ ዝውውሩ በስራ ክፍሎች ላይ የባለሙያ ክፍተት ከፈጠረ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያመጣ ስለሚችል ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፡፡

3. የኢንሹራንስ፣ የባህር ትራንስፖርት እና ሌሎች ወጪዎችን (IFO) በተመኑ መሰረት አለማስላት

በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማምን መመሪያ ቁጥር 158/2011 አንቀጽ 14፣ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ሀ፣ ለ እና ሐ መሰረት ክፍያዎች በተጨባጭ ማስረጃና መረጃ ሊተመኑ ካልቻሉ ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት ወጪ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያ ወጪዎች እንዲሁም የኢንሹራንስ ወጪ ዲክሌር በተደረገው የእቃ ኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ ላይ በቅደም ተከተል 5 በመቶ፣ 5 በመቶ እና 2 በመቶ (በድምሩ 12 በመቶ) በመጨመር በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ እንዲካተት ይደረጋል፡፡ ከህላፊዎች በተሰጠን መረጃ መሰረት የቀረቡት ኢንቮይሶች ተቀባይነት ካገኙ ግን የIFO ወጭዎች ከላይ በተቀመጡት ምጣኔዎች ተሰልተው በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታሉ፡፡ እነዚህን ወጪዎች በተመኑ መሰረት በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ሳያካትቱ መስራት መንግስት ከቀረጥና ታክስ ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ያሳጣዋል፡፡

ኢንሹራንስን በተመለከተ ከውጭ ምንዛሬ (ዶላር) እጥረት የተነሳ አንደር-ኢንቮይሲንግ የተለመደ እንደሆነ ባለሙያዎች አጫውተውናል። ጉምሩክ የኢንሹራንስ ደረሰኝን አስገዳጅ ስላደረገው ምንም እንኳን አንደር-ኢንቮይስ ቢሆንም ደረሰኙ ተያይዞ ለቀረጥና ታክስ ስሌት ይውላል። ይህም የመንግስትን ገቢ ያሳጣል። እንደባለሙያዎቹ ገለፃ አንደር-ኢንቮይሲንግ በሕግ (በመመሪያ) ስለማይከለከል ጉምሩክ የአምጭዎችን ደረሰኝ (የተጭበረበረ (forged) ካልሆነ በስተቀር) ተቀብሎ መስራት ግዴታው ነው። ይህ በሕግ ሊመለስ የሚችል ክፍተት መሆኑንና ሕግ (ፍርድ ቤት) ላይ ያለ ጉዳይ እንደሆነ ገልፀዋል።

ለዚህ ብልሹ አሰራር መከሰት ምክንያቶች ተደርገው የተነሱት በንፅፅር ከIFO የሚሰበሰበው ቀረጥ እና ታክስ ኢምንት ነው በሚል በድህረ ዕቃ አወጣጥ ብዙ ትኩረት አለማግኘት እና በንዝህላልነት (ignorance) እነዚህን ወጪዎች ሳያካትቱ የሚሰሩ ባለሙያዎች መኖር ናቸው።

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ በሁሉም የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በየቀኑ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ገቢ ዕቃዎች ይስተናገዳሉ - በዚህ ሂደት ውስጥ የIFO ወጭዎችን በተገቢው መንገድ አለማስላት የመከሰት እድል ከፍተኛ ነው። ከጉምሩክ ኮሚሽን ኤክስፐርቶች ጋር ካደረግነው ሀሳብ የማጎልበት ውይይት ባገኘነው መረጃ መሰረት ይህ አደጋ የሚያስከትለው ጉዳት ዝቅተኛ ነው (በመንግስትን ገቢ ላይ የሚያስከትለው ተፅእኖ አነስተኛ ነው)። ስለዚህ የስጋቱ ደረጃ መካከለኛ ነው።

እንደ ማሻሻያ እርምጃ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ክፍል ዋጋ ላይ ክትትል እንደሚያደረገው ሁሉ IFO ላይም ትኩረት ሰጥቶ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል። መንግስትም አንደር-ኢንቮይሲንግን በተመለከተ ሕግ (መመሪያ) ሊያወጣ ይገባል። አንደር-ኢንቮይሲንግ የፈጠረው ክፍተት እስከሚስተካከል ድረስ ጉምሩክ ሚኒመም ኢንሹራንስ ቫልዩ አስቀምጦ ቀረጥና ታክስ ቢያሰላ ጊዜያዊ መፍትሄ ይሆናል ብለን እናስባለን።

4. የወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓትን አላግባብ መጠቀም

በአዋጅ 868/መመሪያ 6 ኤክስፖርትን ፕሮሞት ለማድረግ ከተዘረጉት የቀረጥ ነፃ የማበረታቻ ስርአቶች አንዱ ቫውቸር ነው። በዚህ መመሪያ መሰረት ከቀረጥ ነፃ የገቡ ጥሬ እቃዎች ከጉምሩክ መጋዘን እየወጡ ለምርት ተግባር ውለው ኤክስፖርት መደረጋቸውን ጉምሩክ ይቆጣጠራል። አምራቹ ከቀረጥ ነፃ የገቡ ጥሬ እቃዎችን ጥቅም ላይ ካላዋላቸው ወይም ምርት አምርቶ ኤክስፖርት ካላደረገ ጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከ50% ቅጣት ጋር ማስከፈል ይገባዋል። ይህን ተከታትሎ አለማስፈፀም መንግስት ሊያገኘው የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ከማሳጣቱም ባሻገር ለሙስና/ህገ-ወጥ አሰራር በር ይከፍታል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ቢል ኦፍ ኳንቲቲ ነው። የኢንዱስትሪ ሚንስቴር ቢል ኦፍ ኳንቲቲ (ለምሳሌ በ10 ኪሎ ጥሬ ዕቃ ምን ያህል ምርት እንደሚመረት) አወሳሰን ላይ ችግሮች

ይስተዋላሉ። ለዚህም እንደ ማሳያ የሚጠቀሰው ቢል ኦፍ ኳንቲቲ በተደጋጋሚ ማስተካከያ ተደርጎበት የሚመጣ መሆኑ ነው። አንዳንዴ በስንት መከራ በተገኘ የውጭ ምንዛሪ ተገዝቶ የገባ ዕቃ ለምርት ከመዋሉ በፊት ኤክስፓየር ያደርጋል፣ በሌላ በኩል ደግሞ አምራቹ በበለጠ አምርቶ ወይም እራሱ ጥሬ ዕቃውን ለአገር ውስጥ ገበያ የማቅረብ ሁኔታም አለ። ይህ ደግሞ ነፃ የገበያ ውድድር ስርአትን ሊያዛባ ይችላል። ሌላው ጉዳይ ደግሞ በሀገር ውስጥ ተመርተው ወደ ውጪ የሚላኩ ዕቃዎች ዘርፉን ለማበረታታት ሲባል ቀረጥ እንዲከፍሉ ስለማይገደዱ እንደሌሎቹ ገቢ ዕቃዎች ዋጋቸው ተጠንቶ በECVS ዳታ ቤዝ ውስጥ አለመግባቱ ነው። ይህንኑ ተገን በማድረግ ላኪዎች ወደ ውጭ የተላኩ ዕቃዎች በውጭ ሀገር የተሸጡበትን የዶላር ዋጋ በማሣነስ የሚያሳውቁበት ሁኔታ ይስተዋላል። ይህም መንግስት ማግኘት በሚገባው የውጭ ምንዛሪ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያስከትላል።

የተጠናከረ የቁጥጥርና ክትትል ተግባር አለመኖር በዋነኝነት ለዚህ ችግር መንስኤ ነው። የቀረጥ ነፃ መብት ከመሰረቱ በተለያዩ አካላት የሚሰጥ ከመሆኑ አንፃር በአግባቡ መተግበራቸውን የሚከታተል፣ የሚደግፍና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚያስተባብር የረባ ቁመና ያለው አደረጃጀት አለመኖር ችግሩን አባብሶታል። አብዛኛዎቹ የቫውቸር ተጠቃሚዎች እንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ አምራቾች እንደመሆናቸው መጠን በኢንዱስትሪ ልማት ኮርፖሬሽን እና በጉምሩክ መካከል በቂ ቅንጅት አለመኖርም በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ነው። በተጨማሪም አግባብ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት አይቶ እንዳላዩ የማለፍ ሁኔታ ሊከሰት ይችላል።

<u>የስጋት ደረጃ</u>፡- ከጉምሩክ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ሀላፊዎች/ሰራተኞች ጋር ከተደረጉ ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች እንዲሁም ሀሳብ የማጎልበት ውይይቶች የተገኙ መረጃዎች የቀረጥ ነፃ መብቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸዉን ቢያሳዩም ታክስና ቀረጥ ከፍለው ከሚስተናገዱ ገቢ ዕቃዎች ጋር በንፅፅር በቁጥር አነስተኛ ስለሆኑ የጥሰቶች የመከሰት ዕድልም አነስተኛ ነው ብሎ መናገር ይቻላል። ስጋቱ ቢከሰት መንግስት ሊያገኘው የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በከፍተኛ ደረጃ ያሳጣል፣ ነፃ የገበያ ውድድር ስርአትን ያዛባል፣ ለሙስና/ህገ-ወጥ አሰራር በር ይከፍታል። ከዚህ በመነሳት የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው ማለት እንችላለን። ስለዚህ በሪስክ ሜትሪክስ ደረጃ አመዳደብ መሰረት የስጋቱ ደረጃ መካከለኛ ነው።

የቁጥጥርና ክትትል ስርአቱን ማጠናከር፣ የቀረጥ ነፃ መብቶች በአግባቡ መተግበራቸውን የሚከታተል፣ የሚደግፍና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚያስተባብር አደረጃጀት ተግባራዊ ማድረግ፣ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ልማት ኮርፖሬሽን እና በጉምሩክ ኮሚሽን መካከል ያለውን ቅንጅት ማጠናከር ወሳኝ የማሻሻያ እርምጃዎች ናቸው። በተጨማሪም በወጪ ዕቃዎች ላይ ትክክለኛ የዋጋ ዳታ ቤዝ በማደራጀት የተመረቱ ዕቃዎች እንደየጥራት ደረጃቸው ተለይተው ወደሚመለከታቸው ሀገሮች በትክክለኛ ዋጋ እንዲወጡ የሚደረግበት አሰራር መቀረፅ አለበት። የኢንዱስትሪ ሚንስቴርም ቢል ኦፍ ኳንቲቲን እንደ ግብአቶቹ (ዕቃዎቹ) አይነት በተደራጀ መልኩ በባለሙያዎች በማስጠናት መወሰን ይገባዋል።

5. የተገልጋዮች ስምምነት ቻርተርን ያላማከለ የገቢ ዕቃዎች ፍተሻ

ማብራሪያ፦ ይህ ስጋት የተገልጋዮች ስምምነት ቻርተር ላይ በተቀመጠው የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት ፍተሻ አለማድረግን/አለማጠናቀቅን ይመለከታል።

ለችግሩ መከሰት እንደ ምክንያትነት ከተነሱት ጉዳዮች መካከል የክትትልና ቁጥጥር ማነስ፣ የሰራተኞች አቅም ክፍተት፣ ፍራቻ እና በራስ አለመተማመን፣ የስራ ብዛትና ያለው የሰው ሀይል አለመመጣጠን፣ ልዩ ሙያዊ ዕውቀት ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች ተዛማች የትምህርት ዲሲፕሊን ያላቸው ሰራተኞች አለመኖር (ለምሳሌ፦ ለጨርቅ በጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ የሰለጠነ፣ ለመኪና መለዋወጫ በአውቶሞቲቭ የሰለጠነ፣ ለኬሚካል በኬሚስትሪ የሰለጠነ)፣ የቻርተሩ የዕቃዎችን ባሕሪ ከግምት ዉስጥ አለማስገባት (ለምሳሌ ለቁሳቁስ እና ማሽነሪ ተመሳሳይ ስታንዳርድ) እንዲሁም የስነ-ምግባር ችግር (የአገልግሎት አሰጣጡን በማጓተት የድርድርና የሌብነት ስራ ላይ ለመሰማራት) ተጠቃሽ ናቸው።

የስጋት ደረጃ፦ ምንም እንኳን በጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውስጥ በየቀኑ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ገቢ ዕቃዎች ቢስተናገዱም ፍተሻ የሚደረግባቸው (20% ናሙና ተወስዶ) የስጋት ደረጃቸው ቀይ የሆኑት ተለይተው በመሆኑ የፍተሻ መጓተት/መዘግየት እድል አነስተኛ ነው። አደጋው ከደረሰ በቀጥታ የሚሰበሰብ ገቢ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል፣ የተገልጋዮችን እምነት ይሸረሽራል፣ የአገልግሎት አሰጣጡ መጓተትም ዕቃዎች ወደሚፈለጉበት ቦታ በታሰበበት ጊዜ እንዳይሄዱና የሀገር ውስጥ እጥረት እንዲከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፣ ለብልሹ አሰራርም በር ከፋች ነው። ስለዚህም ይህ ስጋት የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው። የመከሰት ዕድል እና የተፅእኖ ጥምረት የስጋቱን ደረጃ መካከለኛ ያደርገዋል።

ቀልጣፋና ፍትሀዊ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት ይቻል ዘንድ ሰነድ ከተመራበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚደረገውን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር ወሳኝ ተግባር ነው። ከሰው ሀይል አንፃርም የፍተሻ ሰራተኞች የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን በመደበኛ መልክ እንዲያገኙ ማድረግ እንዲሁም ለፍተሻ ልዩ ሙያዊ ዕውቀት የሚያስፈልጋቸውን ዕቃዎች ለይቶ በመስኩ ባለሙያተኞችን ማሰልጠን፣ ገበያ ላይ ከተገኙም መቅጠር ችግሩን በተወሰነ መልኩ ይቀርፋል። ቻርተሩ ላይም የዕቃዎችን ባሕሪ ከግምት ዉስጥ ያስገባ ማሻሻያ ቢደረግ መልካም ነው። ያለበቂ ምክንያት የፍተሻ ሂደቱን የሚያጓትቱ እና በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የማይፈትሹ ሰራተኞች ላይ የተጠናከረ እርምጃ መውሰድም ይገባል።

6. ታክስ ያልተከፈለባቸው ዕቃዎች ከህጋዊዎቹ ጋር ተቀላቅለው መግባት/መውጣት

ማብራሪያ፦ ይህ ስጋት በህጋዊ መንገድ ወደ ሀገር በሚገቡ እንዲሁም ወደ ውጭ በሚላኩ ዕቃዎች ውስጥ በመደበቅ በህገ-ወጥ መንገድ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትን ወይም ወደ ውጭ መላክን ይመለከታል።

ለነዚህ ስጋቶች መከሰት አስተዋፅኦ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል በድንገተኛ ፍተሻ እና ኢንተለጀንስ ክፍሎች/ባለሙያዎች የስጋት ደረጃቸው መካከለኛና ዝቅተኛ በሆኑ የቀረጥ ነፃ

እቃዎች እንዲሁም ለንግድ አላማ በማይውሉ ዕቃዎች ላይ ትኩረት አለመሰጠቱ ተጠቃሽ ነው፡፡ በተጨማሪም የወጪ ንግድ ዕቃዎች ላይ የላላ ቁጥጥር እና ክትትል የሚደረግ መሆኑ እንደ ምክንያትነት ሊቀርብ ይችላል፡፡ በድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በፍተሻ ስራዎች ላይ ለሙስናና ብልሹ አሠራር ክፍተት የሚፈጥሩ ስጋቶችን ለመከላከል የተካሄደ የአሠራር ስርዓት ማሻሻያ ጥናት እነዚህ በምክንያትነት የቀረቡትን ሀሳቦች ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ የኢንተሊጀንስና የድንገተኛ ፍተሻ መረጃ በሲስተም የተደገፈ አለመሆን (መረጃው በኤክሴል ነው የሚያዘው) እንዲሁም የስነ-ምግባር ጥሰት (የድንገተኛ ፍተሻ ባለሙያው ከፈተሸ በኋላ ሌላ የሚፈትሽ አካል ስለሌለ ሆን ብሎ የማጭበርበር ተግባር) እነዚህን አደጋዎች ያጎሏቸዋል፡፡

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ ከጉምሩክ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ኤክስፐርቶች ጋር በተደረጉ ሀሳብ የማጎልበት ውይይቶች መሰረት ይህ ስጋት የመከሰት ዕድሉ ከፍተኛ ነው (በሺዎች የሚቆጠሩ ከቀረጥ ነፃ ገቢ ዕቃዎች፣ ለንግድ አላማ የማይውሉ ገቢ ዕቃዎች እንዲሁም ወጪ ንግድ ዕቃዎች ከመኖራቸው አንፃር)፡፡ አደጋው ከደረሰ መንግስት ከቀረጥና ታክስ የሚያገኘውን ገቢ ያሳጣዋል፣ ያልተፈቀዱ/ያልተመረመሩ ምግብ ነክ ዕቃዎች እንዲሁም የሀገር ደህንነት ላይ ስጋት የሚፈጥሩ የጦር መሳሪያ እና ሌሎች ነገሮች በድብቅ ሊገቡ ይችላሉ፣ ዕቃዎች ከጫት ጋር በሕገ-ወጥ መንገድ በትርፍነት ተጭነው ከሀገር መውጣት መሰብሰብ የሚችለውን የውጭ ምንዛሬ ያሳጣል፡፡ ከዚህም በመነሳት ይህ ስጋት የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ የስጋቱ ደረጃ ከፍተኛ ነው፡፡

ስጋቶቹን ለመቀነስ ድንገተኛ ፍተሻ እና ኢንተለጀንስ ክፍሎች ተገቢ የመረጃ፣ የክትትልና የፍተሻ ስራ ዕቃው ምንም ይሁን ምን (ንግድ ያልሆኑ ዕቃዎች፣ የወጪ ንግድ ዕቃዎች ወይም በመካከለኛና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የተመደቡ የቀረጥ ነፃ እቃዎች) በተጠናከረ መልኩ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የኢንተለጀንስና የድንገተኛ ፍተሻ መረጃ በሲስተም የተደገፈ ቢሆን አግባብ ያልሆኑ ድርጊቶችን ለመከታተል ያመቻል፡፡

7. በመመሪያው የጊዜ ገደብ መሰረት ለአቤቱታዎች ውሳኔ አለመስጠት

ለዚህ ስጋት መከሰት አስተዋፅኦ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት የአቤቱታ ማጣራት ሂደት ውስብስብነት እና በአቤቱታ አቅራቢዎች በኩል አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችና መረጃዎችን ማቅረብ ላይ ያለ ክፍተት ናቸው፡፡

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ ከጉምሩክ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ኤክስፐርቶች ጋር በተደረጉ ሀሳብ የማጎልበት ውይይቶች መሰረት ይህ ስጋት የመከሰት ዕድሉም የሚያስከትለውም ጉዳት (መንግስት በወቅቱ ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ማድረግ፣ ደንበኛውን ለእንግልት መዳረግ) በመካከለኛ ደረጃ ይመደባል፡፡ ስራው በቲም ስለሚሰራ ውሳኔ በሙስና ድርድር የመሰጠቱ ዕድል ያን ያህል ነው፡፡

ስጋቱን ለመቀነስ የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍልን አቅም እና ብቃት ማዳበር የግድ ይላል፡፡ በተጨማሪም ውሳኔ አሰጣጥን የሚያቀላጥፉ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎችና

መረጃዎችን በተመለከተ ለአቤቱታ አቅራቢዎች በቂ ግንዛቤ መስጠት የውሳኔ አሰጣጡን ሊያቀላጥፈው ይችላል።

8. መመሪያን የጣሰ በጊዜያዊነት ከሀገር የወጡ ወይም የገቡ ዕቃዎች አስተዳደር

ዕቃዎች በዋስትና ስለሚለቀቁበት ሁኔታ የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 37/2002 አንቀጽ 9/ለ ዋስትና ተመላሽ ወይንም ቀሪ የሚሆነው በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ዕቃ በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ተመልሶ ከአገር ለመውጣቱ ማረጋገጫ ሲቀርብ መሆኑን ይገልፃል። እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1160/2012 አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 12 በጊዜያዊነት ወደአገር ውስጥ የገባ ዕቃ ተመልሶ ከአገር ያልወጣ ወይም የጉምሩክ ሥነ-ስርአት ተፈፅሞበት አገር ውስጥ እንዲቀር ያልተፈቀደለት እንደሆነ ዕቃው ይወረሳል ተብሎ ተደንግጓል። ስለዚህም በጊዜያዊነት ወደ ሀገር በዋስትና የገባ ዕቃ ተመልሶ ወደ ውጭ ስለመውጣቱ/በጊዜያዊነት ከሀገር የወጣ ዕቃ ስለመመለሱ የሚያስረዳ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ በዋስትና ተይዞ የነበረን ገንዘብ ተመላሽ ማድረግ፣ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች ዋስትና ተይዞ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የቆይታ ጊዜያቸው የተጠናቀቀ ቢሆንም እርምጃ አለመውሰድ የተሳሳቱ ተግባራት ናቸው። የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት የ2013 በጀት የ1ኛ እና 2ኛ ሩብ ዓመት ኦዲት ሪፖርት እነዚህ ጥሰቶች መከሰታቸውን ዘግቧል።

ከጉምሩክ ኮሚሽን ኤክስፐርቶች ጋር በተደረጉ ሀሳብ የማንልበት ውይይቶች በተረዳነው መሰረት ዕቃዎች በጊዜያዊነት ከሀገር ሲወጡ/ሲገቡ በመግቢያ በሮች ላይ የሚጠየቁት ሰነዶች ላይ ትልቅ ክፍተት አለ (ለምሳሌ አንዳንዶቹ የመግቢያ በሮች በጊዜያዊነት ዕቃዎች ሲወጡ የሚሰጠው የመውጫ ሰነድ (T1) ላይ ምልክት በማድረግ ብቻ ያስተናግዳሉ፣ ሌሎች ደግሞ የኢምፖርት ሰነድ (IM6) አስሞልተው ያስተናግዳሉ)። ይህ የሚያሳየው አሰራሩ ወጥነት እንደሚጎለው ነው። ሌላው ጉዳይ ደግሞ በጉምሩክ መመሪያ መሰረት አንድ ዕቃ (ለምሳሌ ተሽከርካሪ) ለስራ ከአገር ሲወጣ ሰነድ ሞልቶ ነው፣ ሲመለስም የኢምፖርት ሰነድ መሙላት አለበት። ከውይይት ያገኘነው መረጃ የሚያሳየው አንዳንድ የቆይታ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ዕቃዎች የኢምፖርት ሰነድ ሳይዙ በአንድ በር ወደ ሀገር ተመልሰው ይገቡና ስራ ይሰራሉ። በአንድ አጋጣሚ ለተመሳሳይ ስራ ተመልሰው ሊወጡ ሲሉ በዚህ ጊዜ ወጥተህ ነበር፣ መመለስህን ሰነድ አቅርበህ ክሊር አላደረክም ተብሎ ነው የሚያዙት። በአጠቃላይ እነዚህ ክፍተቶች የመጡት ዕቃዎች ሲገቡና ሲወጡ በመግቢያ በሮች በምን መንገድ መስተናገድ እንዳለባቸው የሚገልፅ አሰራር ባለመኖሩ ነው። ይህንን ለመቅረፍ ከሀገር በጊዜያዊነት ወጥተው የሚመለሱ ዕቃዎችን በተመለከተ መመሪያ እየተዘጋጀ መሆኑን የውይይቱ ተሳታፊዎች ገልጸውልናል።

ከዋስትና ገንዘብ አስተዳደር ጋር በተገናኘ ለሚከሰቱ ብልሹ አሰራሮች እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉት፦ የገቢ ተሰብሳቢና ዋስትና ሒሳቦች አስተዳደር የስራ ክፍል ተከታትሎ የማስፈጸም ክፍተት፣ የቁጥጥር መላላት፣ ተገቢ ሰነዶችን አስቀርቦ ስራን በተገቢው መንገድ አለመስራት (ignorance)፣ በዋስትና አስተዳደር ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች ክህሎት ማነስ (የማይሆኑ ሰነዶች ቀርበው ተሰርቶ ሊሆን ስለሚችል)፣ እና ስነ-ምግባር ችግር (ሰራተኛው ሪስክ ወስዶ በድርድር አድርጎት ሊሆን ስለሚችል) ናቸው።

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ ከተለያዩ ሰነዶች እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ኤክስፐርቶች ጋር ካደረግነው ውይይት በመነሳት የዚህን ብልሹ አሰራር የመከሰት እድል ዝቅተኛ ደረጃ ሰጥተነዋል። ይህ ስጋት ከተከሰተ መንግስትን ከፍተኛ ገቢ ያሳጣዋል፣ በጊዜያዊነት ከቀረጥ ነፃ ገብተው የቆይታ ጊዜያቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በሀገር ውስጥ ንግድ እንቅስቃሴ መሳተፋቸው ፍትሀዊ የንግድ ውድድርን ያዛባል፣ ሀገር ውስጥ መቅረት የሌለበት ዕቃ አገር ውስጥ በመቅረቱ ሀገርን ሊጎዳ ይችላል፣ ከሀገር ወጥቶ መቅረት የሌለበት ዕቃም እንደወጣ ሳይመለስ ሊቀር ይችላል። ይህም የጉዳቱን መጠን ከፍተኛ ያደርገዋል። የመከሰት ዕድል እና የተፅእኖ ጥምረት የስጋቱን ደረጃ መካከለኛ ያደርገዋል።

የገቢ ተሰብሳቢና ዋስትና ሒሳቦች አስተዳደር የስራ ክፍል ተከታትሎ የማስፈጸም አቅሙን ማሳደግ፣ የክትትል እና ቁጥጥር ስርአቱን ማጠናከር (በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ለሌላ አገልግሎት እንዳይውሉ)፣ ለሰራተኞች የክህሎት ማበልፀግያ ስልጠና መስጠት፣ ህገወጥ ስራ ላይ በተሰማሩ ሰራተኞች ላይ አስተማሪ የሆነ እርምጃ መውሰድ፣ እንዲሁም ዕቃዎች በጊዜያዊነት ሲገቡና ሲወጡ በመግቢያ በሮች በምን መልኩ መስተናገድ እንዳለባቸው የሚገልፅ መመሪያ/ደንብ ነድፎ በስራ ላይ ማዋል ወሳኝ የማሻሻያ እርምጃዎች ናቸው ብለን እናምናለን።

9. ሰነድ አልባ እና ገደብ/ክልከላ የተደረገባቸውን ዕቃዎች በመመሳጠር በኬላ ማሳለፍ

<u>ማብራሪያ</u>፦ ይህ ስጋት ሰነድ አልባ ዕቃዎችን በመመሳጠር በኬላ ማሳለፍን፣ ወደሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለን ወይም ገደብ የተደረገበትን ዕቃ በአግባቡ ሳይፈትሹ በኬላ ማሳለፍን እንዲሁም ዕቃ የመቀነስ/የማጉደል ስራን (ቅሸባ) ይመለከታል።

ለችግሩ መከሰት እንደ ዋነኛ ምክንያትነት የተነሱት፦ ኬላ አካባቢ ጠንካራ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር፣ የስነ-ምግባር ችግር (የንግድ እንቅስቃሴውን ለማቀላጠፍ (ፋሲሊቴሽን) የሚሰሩ ሠራተኞች እና የቁጥጥር ሥራውን የሚሰሩ ሠራተኞች በመመሳጠር ዕቃዎች ተገቢው ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወይም ክልከላ የተደረገባቸው ዕቃዎች እንዲያልፉ የሚያደርጉበት ሁኔታ መኖሩ)፣ የመኪና ቦዲ ፓርቶችን ለቅሸባ እንዲያመች በተራቀቀ መንገድ የመገጣጠም ሕገ-ወጥ ተግባር እንዲሁም የኮንትሮባንድ ንግድን የመከላከል ባህል በሕብረተሰቡ ዘንድ አለመዳበር ናቸው። ከጥልቅ ቃለ-መጠይቅ እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች ባገኘነው መረጃ መሰረት በትራንዚት አካባቢ የሚስተዋለው ሌላው ችግር አንድ ዕቃ ከጅቡቲ ተነስቶ ወደ ሀገር ውስጥ ለመግባት ጉዞ ከጀመረ በኋላ ዕቃው ምንም አይነት ችግር ሳይደርስበት ስለመግባቱ ለማረጋገጥ የሚያስችል በሲስተም የተደገፈ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት አለመኖሩ ነው። ማንኛውም ዕቃ ሲጓጓዝ ዕቃውን በሚያጓጉዘው ተሽከርካሪ ላይ የጂፒኤስ (GPS) ሲስተም ሊገጠምለትና ቁጥጥርም ሊደረግበት እንደሚገባ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 ይደነግጋል። ሆኖም ግን በተለያዩ ምክንያቶች (ለምሳሌ፣ በዋጋው ውድነት የተነሳ) ይህ ተግባራዊ አልተደረገም።

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ በመጠይቁ ውጤት መሰረት 48.1% እና 35.9% የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅደም ተከተል የኮንትሮባንድ ተግባራትን አይቶ እንዳላዩ የማለፍ ተግባር እንዲሁም የሸቀጦችን ኮንትሮባንድ የማመቻቸት ወይም የማደራጀት ተግባር እንደሚፈፀም ሙሉ ወይም መጠነኛ ስምምነታቸውን ገልፀዋል። ይህን ግኝት ከተለያዩ ሰነዶች (ለምሳሌ ጉምሩክ ኮሚሽን በ2013 እና በ2014 በጀት ዓመት የተስተዋሉ ዋና ዋና የስነ-ምግባር ክፍተቶች ብሎ ያወጣቸው ሪፖርቶች) እና ከጥልቅ ቃለ-መጠይቅ ከተገኙ ፍሬ ሀሳቦች ጋር በማዋሃድ የዚህን ብልሹ አሰራር የመከሰት እድል መካከለኛ ደረጃ ሰጥተነዋል። ይህ ስጋት ከተከሰተ መንግስት ማግኘት ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳያገኝ ያደርጋል፣ የኮንትሮባንድ ቁጥጥር እንዲከስም በማድረግ የህብረተሰቡን ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል፤ ህጋዊ የንግድ ውድድር ስርዓትም እንዳይኖር ያደርጋል። ከዚህም በመነሳት ይህ ስጋት የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው። ስለዚህ በሪስክ ሜትሪክስ ደረጃ አመዳደብ መሰረት የስጋቱ ደረጃ ከፍተኛ ነው።

ኬላዎች አካባቢ ጠንካራ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ቀጣይነት ያለዉ የህገ-ወጥ ንግድና የኮንትሮባንድ መከላከል ስልት ቀይሶ መተግበር፣ የኮንትሮባንድ ንግድን የመከላከል ባሕል እንዲዳብር ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በተጠናከረ መልኩ መስጠት እንዲሁም የጉምሩክ ማህተሞችን (customs seals) አስመስለው በመስራት የቅሸባ ተግባር የሚፈጽሙት ላይ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ ስጋቱን ለመቀነስ የመፍትሔ ሀሳቦች ናቸው። በተጨማሪም መንግስት ካርጎ ትራኪንግ/ጂፒኤስ ቴክኖሎጂን በስራ ላይ እንዲያውል እንመክራለን (የሙስና ስጋቱ ሊያደርስ ከሚችለው ጉዳት የበለጠ ዋጋ ሊያስከፍል አይገባም የሚለው መሰረተ ሀሳብ እንደተጠበቀ ሆኖ)።

4.2. የሙስና ስጋቶች በገቢዎች ንዑስ-ዘርፍ

1. በስልጣን አላግባብ በመገልገል ታክስ/ግብር መሰወር

በገቢዎች ዘርፍ ከሚያስጉ የሙስና አይነቶች ዋነኛው በስልጣን አላግባብ መገልገል እንደሆነ ይህ ጥናት ያሳያል። ከዳሰሳ መጠይቅ፣ ጥልቅ ቃለ-መጠይቅና ሰነዶች በተገኘው መረጃ መሰረት ከስጋቱ መገለጫዎች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ። የግብር ሰብሳቢ ባለሙያዎች ስልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም አንድ ግብር ከፋይ ሊከፍል የሚገባውን የግብር መጠን እንዲያሳንስ/እንዲያስቀር ያደርጋሉ። ይህም የሚደረገው ወጪዎችን አላግባብ በማናር እና ገቢዎችን በማሳነስ ትርፍ በማሳነስ (የገቢ ግብር ትርፍ ላይ ስለሚሰላ)፣ ዕቃው/ንብረቱ የተገዛበትን እውነተኛ/ትክክለኛ ዋጋ በማሳሳት/በማሳነስ፣ የግብር ከፋይነት ደረጃን ሃሰተኛ ሰነድ በመጠቀም ዝቅ በማድረግ (ደረጃ “ለ” የነበረን ደረጃ “ሐ” እንደሆነ በማቅረብ)፣ የግብር ከፋይነት ደረጃን በማጭበርበር (ወደ “ለ” ማደግ ሲገባዉ “ሐ” ላይ ማቆየት)፣ የግብር እፎይታ ጊዜዎችን በማጭበርበር፣ ከግብር-ነፃ ሃሰተኛ ሰነዶችን በመጠቀም፣ የቀን ገቢ ግምት በማሳነስ፣ ወዘተ… ናቸው።

ከጥልቅ ቃል-መጠይቆች ባገኘነው መረጃ መሰረት አንዳንድ የስራ ክፍሎች ዉስጥ (ለምሳሌ ታክስ ኦዲት) የሚሰሩ ባለሞያዎች በሀላፊነታቸው ተጠቅመው እንደፈለጉ ለማድረግ የሚያስችላቸው ክፍተት አለ፣ ምክንያቱም ስራው አዉቶሜትድ አይደለም (ማንዋል ነዉ)፤ ግብር ከፋዩ ደግሞ የመረጃ አያያዝ ችግር አለበት፤ ባለሞያዉም የፈለገዉን የመያዝና የመጣል ሁኔታ ይኖራል፣ ይህም ለሙስና በር ይከፍታል።

የእፎይታን ጊዜን በተመለከተ አብዛኛዎቹ የጥልቅ ቃለ-መጠይቅ ተሳታፊዎች ጭራሹኑ ቢዘጋ (ባይፈቀድ) የሚል ሀሳብ አቅርበዋል። በነዚህ መላሾች አስተያየት መሰረት ሀገር በግብር እፎይታ ጥቅም እያገኘች ሳይሆን በከፍተኛ ሁኔታ እየተጎዳች ነዉ፣ እፎይታም እንደ አንድ ኢንቨስትመንት tool አላግባብ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው። ይህ ካልተቻለም የግብር እፎይታ ከተጽዕኖ (impact) አንፃር ተለየተዉ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ለሆኑት ለሃገርቱ ገቢ (income) የሚያመነጩ ዘርፎች ላይ ብቻ መፈቀድ አለበት ብለዋል። ይህም ቢሆን የግብር እፎይታ ጊዜው ቢያጥር፣ እንደገናም የመታደስ ሁኔታ ቢቀር የተሻለ እንደሚሆን ሙያዊ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ከዳሰሳ መጠይቅ በተገኘዉ ዉጤት መሰረት በስልጣን አላግባብ ለመገልገል እንደ ምክንያትነት ከተነሡት ዉስጥ የተቋማቱ ሠራተኞች የታክስ መጠን አወሳሰን ላይ ያላቸዉ ስልጣን ከፍተኛ መሆን (79.6%)፣ የተቋማት ተደራራቢ ወይም ግልጽ ያልሆነ ሀላፊነት (mandates) የደንቦችን አተገባበር እና ማስከበር ወጥነት (consistency) ማዳከም (77.2%)፣ እንዲሁም ግልጽነትና ወጥነት የጎደላቸው የታክስ ህጎች በስርዓቱ ውስጥ ክፍተቶችን ማስከተል (75.8%) ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ። ይህ አሀዛዊ መግለጫ ከ537 የጥናቱ ተሳታፊዎች የተጠናከረ ነው። በተጨማሪም ለግብር/ታክስ ሥወራ እንደ ምክንያትነት ከተጠቀሱት መካከል የሂሳብ ባለሙያዎች፣ የግብር ሰብሳቢዎች፣ የባለ-ሃብቶች፣ ወዘተ.. የስነ-ምግባር ችግር/ውድቀት ይገኝበታል። እነዚህ የተጠቀሱት አካላት በመመሳጠር በስልጣን አላግባብ በመጠቀም እንደሚያጭበረብሩ ጥናቱ ያሳያል። ግብር ከፋዮች የግብር ህጎች ላይ ያላቸው ግንዛቤና ዕውቀት ማነስ እንዲሁም የግብር አሰባሰብ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ በቴክኖሎጂ አለመታቀፍ (ቢኖርም አለመጠቀም) ሌሎች ለስጋቱ እንደ መንስዔነት ከተጠቀሱት ውስጥ ይገኙበታል።

<u>የስጋት ደረጃ፦</u> ከመጠይቁ ቀመር ውጤት (ከላይ በዝርዝር የተገለፀው)፣ ከሰነዶች እና ከጥልቅ ቃለ-መጠይቆች እንደተረዳነው በስልጣን አላግባብ መጠቀም ብልሹ አሰራር የመከሰት እድሉ ከፍተኛ ነው። ይህ ስጋት የገቢዎች ዋና ተግባር የሆነውን ግብር/ታክስ መሰብሰብን ሊያስተጓጉል ይችላል፣ ስልጣናቸዉን አላግባብ የሚጠቀሙ የተቋሙ ሠራተኞች ካሉ መሰብሰብ ያለበት ግብር/ታክስ እንዳይሰበሰብ በማድረግ ከባድ ጉዳት በተቋሙም በሃገሪቱ ላይም ያመጣል። በተጨማሪም ምግባረ-ብልሹ የግብር ሰብሳቢ ሰራተኞች እና ግብር ከፋዮች እንዲንሰራፉ ያደርጋል። ከተጠቀሱት ነጥቦች በመነሳት ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት ከባድ ነው ማለት እንችላለን። ስለዚህ የስጋቱ ደረጃ ከፍተኛ ነው።

ይህን ስጋት ለመቀነስ ብሎም ሀገሪቱ ከግብር እና ታክስ የምትሰበስበውን ገቢ ለመጨመር የብልሹ አሰራሩን ምክንያቶች/ክፍተቶች መድፈን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም ማንኛውንም በግብር ሰብሳቢ ባለሙያዎች እና ሌሎች ተዋናዮች (የሂሳብ ባለሙያዎች፣ ግብር ከፋዮችና ኦዲተሮች) መካከል ያለውን ህገ-ወጥ የግንኙነት ሰንሰለቶችን መከታተልና መቁረጥ፣ ግብር ከፋዩና ታክስ ኦዲተሩ እንዳይገናኙ የሚያደርግ አሰራር ስርአት መዘርጋት፣ የግብር ስብሰባ ሥራውን ማዘመን (በቴክኖሎጂ)፣ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት (ታክስ-ነፃ እና እፎይታ ፈቃድ ሰጪዎች) ጋር ተባብሮ/ተናቦ መስራት እንዲሁም የግብርን ሀገራዊ ፋይዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት የመፍትሄ ሀሳቦች ናቸው ብለን እናምናለን፡፡

2. የመረጃ ደህንነት ስጋት

የመረጃ ደህንነትን አስመልክቶ በጥልቅ ቃለ-መጠይቅ እና በሌሎች መንገዶች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየዉ በአዲስ አበባና በተመሳሳይ ከተሞች በሚገኙ የግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ውስጥ አውቶሜትድ ሲስተሞች (ሲግታስና አይቤክስ፣ ለደረጃ "ሐ" ደግሞ ኢ-ታክስ) በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋላቸው መረጃ ሚስጥራዊነቱና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን አስተዋፆ ቢያደርግም ሲስተሞቹ ላይ የተወሰነ ክፍተት አለ፡፡ ለምሳሌ ሲግታስ አሁን ላይ አርጅቷል፣ ካሽሮች ወደኋላ በመሄድ ገንዘብ ገቢ ማድረግ ይችላሉ፣ ይህ ደግሞ ያልተገባ የግል ጥቅም ለማግኘት በር ይከፍትላቸዋል፡፡ ራይት ኦፍ እና ካሽ ሪቨርስ አደራረግ ላይም ጥንቃቄ የሚፈልጉበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ ስጋት በቀን ገቢ ግመታ ወቅት ለታክስ ከፋዩ የተቋሙን የውስጥ አሰራር አስቀድሞ በማሳወቅ ታክስ እንዲሰወር በማድረግ፣ የካሽ ሬጅስተር ምስጥራዊ የአሰራር ሲስተምን ለታክስ ከፋዩ አሳልፎ በመስጠት መመዝገብ ከሚገባው በታች እንዲመዘግብ በማድረግ፣ በስነ-ምግባር ችግር የተከሰሱ ሰራተኞችን የዲሲፕሊን መረጃ ከፋይል ውስጥ እንዲወገድ በማድረግ፣ ከግዢ ጋር በተያያዘ ለተወዳዳሪዎች የጨረታ መረጃዎችን አስቀድሞ በመስጠት ያላግባብ የውድድሩ አሸናፊ እንዲሆኑ በማድረግ፣ የመረጃ ሰጭ (whistleblower) መረጃ ለተጠቋሚው አሳልፎ በመስጠት፣ እና በመሳሰሉት መንገዶች ይከሰታል፡፡

ጥናቱ ለዚህ ሙስና አይነት መከሰት ምክንያቶች ብሎ የለያቸው ሶስት ዋናዋና ምክንያቶች የሰራተኞች የስነ-ምግባር ጉድለት፣ የቁጥጥር ስርአት መላላት (ወይም አለመኖር)፣ እና አሰራሮች ዲጂታላይዝ አለመሆናቸው (በተለይ በወረዳዎች እና በዞኖች) ናቸው፡፡

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ በመጠይቁ ትንተና መሰረት 66.1%፣ 25.5% እና 37.1% የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅደም ተከተል የተዘረጉት አውቶሜትድ ሲስተሞች ክፍተት (loopholes) እንዳለባቸው፣ የተወዳዳሪዎችን የንግድ እንቅስቃሴ የተመለከተ የውስጥ መረጃ ለሌላ አካል አሳልፎ እንደሚሰጥ እንዲሁም ፋይሎች እንዲጠፉ/እንዲሰወሩ እንደሚደረግ ሙሉ ወይም መጠነኛ ስምምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ ከነዚህ ግኝቶች እና በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ከተገኘው ውጤት በመነሳት ይህ የሙስና አይነት የመከሰት እድሉ መካከለኛ ነው፡፡ ይህ የሙስና አይነት ተደጋግሞ ቢከሰት የሚፈለገው የግብር መጠን እንዳይሰበሰብ ከማድረግ አኳያ፣ የስራ እንቅስቃሴዎች እና የታለሙ ግቦችን ከማስተጓጎል አኳያ እንዲሁም ብልሹ አሰራር

(ሌብነት) እንዲበራከት በማድረግ ተገልጋዩ በተቋሙ ላይ ያለዉ መተማመን እንዲጠፋ ከማድረግ አኳያ የሚያስከትልው ተፅእኖ መካከለኛ ነው፡፡ ስለዚህ የስጋቱ ደረጃ መካከለኛ ነው፡፡

የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ እንዳይሆን ስራዎችን እና የመረጃ ስርአትን ዲጂታላይዝ ማድረግ፣ ከሥራ የለቀቁ ሠራተኞችን አካዉንት ተከታትሎ መዝጋት፣ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር ኢንተርፌስ በመፍጠር ስራን በቴክኖሎጂ ማዘመን እንዲሁም የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮችን ሶፍትዌር (VAT Automation Sigtas) አልምቶ ወደ ሥራ ማስገባት ይገባል፡፡ ይህንንም ለሁሉም ዞኖች፤ የከተማ መስተዳድሮችና ወረዳዎች ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሰራተኞች ስነ-ምግባር እና ተጠያቂነት ላይ አትኩሮ መስራት ለችግሩ መፍትሄ ነው፡፡

3. ሰነዶችን ማጭበርበር እና ያላግባብ መጠቀም

ጥናቱ እንደሚያሳየው የዚህ ሙስና ስጋት መከሰት ማሳያዎቹ ውስጥ፦ ሃሰተኛ ሰነዶችን በመጠቀም ግብር/ታክስ የመሰወር ድርጊቶች (ግብር ከፋዩ ሀሰተኛ ደረሰኞችን እንዲጠቀም ማመቻቸት)፣ ደረሰኞችን ያለበቂ ምክንያት ቮይድ የማድረግ ሁኔታ፣ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ሳይፈረሙ የማስተላለፍ ድርጊት፣ ከፋይል/ከሰነድ ላይ የሚፈለጉ መረጃዎች አለመገኘት/መጥፋት፣ የካሽ ሬጅስተርን ባግባቡ መጠቀም ካለመቻል የተነሳ ሃሰተኛ ሰነዶችን መጠቀም (የካሽ ሬጅስተር 21 ካራክተር አለው፣ ይህ ደግሞ ለክትትልም ስለማያመች ለሀሰተኛ ሰነድ መበራከት የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል)፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ ለግብር አወሳሰን የሚረዱ መረጃዎችን/ሰነዶችን በወቅቱ ባለማቅረብ የሚፈፀም ብልሹ አሰራርም ከዚሁ ጋር ይያያዛል፡፡ ከፋይናንስና ግዢ አስተዳደር ጋር በተያያዝም ይህ ችግር በብዛት ይታያል፡፡ ለማጣቀሻ ያህል በውሉ specification መሰረት ያልተገዛን እቃ እንዳሟላ አድርጎ ሰነድ ማሰራት፣ ከሂሳብ መደብ ውጪ ተመዝግቦ የተገኘ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ መገኘት እና ተመሳሳይ ችግሮች ይታያሉ፡፡ በተጨማሪም የተጭበረበረ የስራ ልምድ ማስረጃ በሰራተኞች ማህደር ውስጥ መገኘት እና በየአመቱ/በየሩብ አመቱ እንዲሁም በተለያዩ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ተመሳሳይ ሪፖርት መኖር ለሙስና ስጋቱ መገለጫ ናቸው፡፡

ለስጋቱ መከሰት እንደ ምክንያትነት ከቀረቡት ውስጥ የስነ-ምግባር ጉድለት (የግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ሰራተኞች እና የግብር ከፋዮች ህገ-ወጥ ትስስር/መመሳጠር)፣ የቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ አለመዘርጋቱ እና ያለውም ልል መሆኑ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የቅንጅት ክፍተት (ከግብር-ነፃ፣ የእፎይታ ጊዜ፣ ወዘተ ከገቢዎች ቁጥጥር ውጪ ስለሆኑ ከዚህ ጋር የተያያዙ ሃሰተኛ ሰነዶች ሊኖሩ ስለሚችሉ)፣ ከንብረት ጋር የተያያዙ የወጪ እና ገቢ ዕቃዎች ካርዶችን በትክክል አለመጠቀም (ለምሳሌ ቢን ካርድ፣ እስቶክ ካርድ፣ መዝገብ 70ሀ እና ዩዘር ካርድ እያለ በጊዜ አለመመዝገብና አለማቀናነስ)፣ እንዲሁም የተቋሙ ሠራተኞች የመዝገብ አያያዝ ዕዉቀት ማነስ እና በቴክኖሎጂ በበቂ ሁኔታ አለመታገዝ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ ከሁሉም የጥናት ተቋማት እና ቅርንጫፎቻቸው የተገኙ የቃለ-መጠይቅ፣

የሰነድ ማስረጃዎች እና ሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) እንደሚያሳዩት የዚህ ሙስና ስጋት በገቢዎች ዘርፍ የመከሰት እድሉ ከፍተኛ ነው:: ከተከሰተም የሚያስከትለው ተፅዕኖ መሰብሰብ ያለበትን ግብር ከማሳጣት (የዋና ዋና ንብረቶች ወይም ከፍተኛ የገንዘብ ኪሳራ በሀገሪቷ ላይ ከማድረስ) እንዲሁም የሰራተኛውንና የተቋሙን ታማኝነት ከመሸርሸር አንፃር በጣም ከፍተኛ ነው:: ስለዚህ በሪስክ ሜትሪክስ ደረጃ አመዳደብ መሰረት የስጋቱ ደረጃ ከፍተኛ ነው::

ይህን የሙስና ስጋት ለመቀነስ የሂሳብ ባለሙያዎች፣ የግብር ሰብሳቢዎች እና የግብር ከፋዮች ህገ-ወጥ ትስስርን/መመሳጠርን መከታተልና እርምጃ መውሰድ (ቢያንስ የገቢዎች ተቋም የራሱን ግብር ስብሳቢ ባለሙያዎች መከታተል ይችላል)፣ የግብር አሰባሰብ ሂደትን ከእጅ በጅ ወደ ቴክኖሎጂ መቀየር (ሁሉንም የግብር አይነቶች፣ በሁሉም ቅርንጫፎች/ዞኖች/ወረዳዎች)፣ የግብርን ሀገራዊ ፋይዳ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት፣ ከተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት (ንግድ ቢሮ፣ ኢንቨስትመንት ቢሮ፣ ወዘተ..) ጋር ተቀናጅቶ መስራት፣ ግዢዎችን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ፣ እንዲሁም የሰራተኛውን ክህሎት ማሳደግ እንደመፍትሄ ጥናቱ ያስቀመጣቸው ናቸው::

4. ያላግባብ ጉዳይን ማጓተት

በዚህ ጥናት የዳሰሳ መጠይቅ ዉጤት ከ537 መላሾች 62.3% የሚሆኑት ሰው ሰራሽ (artificial) መዘግየቶች በግብር ስርአት ውስጥ ተፈጥረዋል ሲሉ መልሰዋል:: በተጨማሪም በርካታ የጥልቅ ቃለ-መጠይቅ ተሳታፊዎች የግብር ከፋይ መዝገቦች በወቅቱ ተመርምረዉ መፍትሔ አለማግኘታቸውን ተናግረዋል:: ይሄ የሚያሳየዉ ያላግባብ ጉዳይን የማጓተት ሙስና ስጋት በገቢዎች ዘርፍ መኖሩን ነዉ::

ለዚህ የሙስና ስጋት መከሰት እንደ ምክንያትነት ከተነሱት መካከል የግብር አሠራሮች/ሂደቶች ውስብስብነት እና የመመሪያዎች መብዛት (በ71.3% መጠይቅ መላሾች ሙሉ ወይም ከፊል ስምምነት ያገኘ)፣ የተወሰኑ የታክስ ባለሙያዎች/ሰራተኞች የሥነ-ምግባር ችግር፣ የቁጥጥር መላላት፣ ዘመናዊ የግብር አሰባሰብ/አከፋፈል (E-file and E-payment) ለሁሉም አለመዳረሱ፣ በየተቋማቱ ያለው የሰው ሃይል እና ባለጉዳዮች ቁጥር አለመመጣጠን፣ የመብራት እና የሲስተም (network/server) መቆራረጥ እንዲሁም የሰራተኞች ክህሎት ማነስ እና ተነሳሽነት ማጣት በዋነኛነት ተጠቃሽ ናቸው:: በተጨማሪም በሙከራ ስራ ያልታዩ እና ያልተፈተሹ ሲስተሞች ወደ ስራ መግባት እንዲሁም አዲስ ወደ ስራ እየገቡ ያሉ በሲስተም መካተት ያለባቸው የስራ ክፍሎችና ወረዳዎች አለመካተታቸው ስጋቱን አባብሰውታል::

<u>የስጋት ደረጃ</u>፡- ሰው ሰራሽ (artificial) መዘግየቶች በግብር ስርአት ውስጥ መፈጠራቸውን 62.3% መጠይቅ መላሾች ተስማምተውበታል:: በተጨማሪም 62.7%፣ 65.9% እና 57.0% የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅደም ተከተል በተቋማቸው ውስጥ በጣም የተወሳሰቡ ጉዳዮችን የማስተናገድ ልምድ ማነስ መኖሩን፣ ግብር ሰብሳቢዎች ስለ ቀረጥ ህጎች/ኮድ ያላቸው እውቀት

በሚፈለገው መጠን አለመሆኑን፣ እንዲሁም ብቃትን መሰረት ያላደረገ የሰራተኞች ምልመላ በተቋማቸው ውስጥ መኖሩን መስክረዋል። እነዚህ ክስተቶች ለጉዳዮች መጓተት አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ እሙን ነው። ስለዚህ ይህ የሙስና ስጋት የመከሰት እድሉ ከፍተኛ ነው ማለት እንችላለን። ይህ የሙስና ስጋት ግብር በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ያደርጋል፣ በኦዲት ሥራ ላይ ሲያጋጥም የኦዲት ምርመራ ውጤቶችን ያጓትታል፣ በግዢ ክፍል ሲያጋጥም የግዢ ሂደቶችን በማጓተት ሥራዎች በቅልጥፍና እንዳይሰሩ ያደርጋል፣ ብልሹ አሰራር እንዲበራከት በማድረግ ተገልጋዩ በተቋሙ ላይ ያለዉ አመኔታም እንዲሸረሽር ያደርጋል። ከዚህም በመነሳት ተፅዕኖው መካከለኛ እንደሆነ አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ተስማምተውብታል። የሁለቱ ጥምር የስጋት ደረጃውን ከፍተኛ ያደርገዋል።

ለዚህ የሙስና ስጋት መፍትሔ ናቸው ተብለው ከተነሱት መካከል፡- የሠራተኛውን ስነ-ምግባር እና ሙያዊ ብቃት በሥልጠናዎች በማነፅ/በመገንባት ጉዳዮች በተቀመጠው የዜግነት ቻርተር ስታንዳርድ መሠረት በፍጥነት እንዲከናወኑ ማድረግ፣ ዘመናዊ አሰራሮችን ማስፋፋት እና ሁሉም እንዲጠቀም ማስገደድ (E-Payment and E-file systems)፣ የሰራተኞችን ብዛት እና ክህሎት ከተገልጋዩ ብዛት/አይነት አንፃር ማስተካከል እና ተጠያቂትን ሥራ ላይ ማዋል፣ እንዲሁም የመብራት እና ኔትወርክ መቆራረጥን ከሚመለከታቸዉ ባለ-ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ማስተካከል ይገኙበታል።

5. ጉቦ መቀበል

በ537 የጥናቱ ተሳታፊዎች የዳሰሳ መጠይቅ ትንተና መሰረት ከመጠን ያለፈ ግብር መተመን (74.4%)፣ ለሃሰተኛ የተ/እ/ታ ተመላሽ ጥያቄዎች መልስ መስጠት (69.1%)፣ ሂደቶችን ለማፋጠን ክፍያ መጠየቅ (65.7%)፣ ግብር ከፋዮች ገቢያቸዉን እንዲያሳንሱ ማመቻቸት (63%) እንዲሁም ሰዉ ሰራሽ መዘግየቶችን መፍጠር (62.3%) በገቢዎች ስርአት ውስጥ ተስተውለዋል። የግብር ሰብሳቢ ባለሙያዉ እነዚህ ድርጊቶች ዉስጥ የሚገባዉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጥ ፈልጎ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነዉ። ስለዚህ እነዚህ ሁናቴዎች በተዘዋዋሪ ጉቦ መቀበል ከሚባለዉ የሙስና ስጋት ጋር አብረው የሚሄዱ ናቸዉ። በተጨማሪም ጉዳዮችን በፍጥነት ለማስኬድ የተቀመጠ የዜግነት ቻርተር ቢኖርም የግብር ከፋይ መዝገቦችን በወቅቱ አለመመርመር እና መፍትሔ አለመስጠት እንደ ችግር ተነስቷል። ይህ ችግር ከመመሪያዎች መብዛት እና ከሙያ ክህሎት ማነስ ጋር ተያይዞ የመምጣት ዕድል ቢኖረውም ለሙስና ድርድር ሆን ተብሎ የተደረገ አይደለም ብሎ መደምደም ግን አይቻልም። እንዲሁም ሁልጊዜ ከደንበኛ ሰነድ ላይ ስህተት በመፈለግ ላይ ብቻ ማተኮር እና ከባለጉዳዩ ጋር እልህ መያያዝ በሰፊው እንደሚስተዋል የጥልቅ ቃለ-መጠይቅ መላሾች ተናግረዋል። ይህ ተግባር ባለጉዳዩን አጣብቂኝ ዉስጥ በማስገባት ለመደራደር፣ ብሎም ጉቦ ለመቀበል የታለመ ሊሆን ይችላል።

ሌላው የተነሳው ጉዳይ የፌደራል የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አደረጃጀት ነው። እንደጥናቱ ተሳታፊዎች አመለካከት ኮሚሽኑ የሚመለከተዉን ሃላፊነትና ስልጣን ለዉጭ አካል

አሳልፎ ሰጥቷል፣ የሙስናን ጉዳይም ዉጫዊ አድርጎ የመመልከት ሁኔታ አለ። በዚህም የተነሳ በተገኙ ግኝቶች ላይ በቂ እርምጃ እየተወሰደ አይደለም ብለዋል። የተያዙ ጥፋኞች ለፖሊስ/ለህግ ከቀረቡ በኃላ ምን ሆኑ፣ ጉዳዩስ ከምን ላይ ደረሰ የሚሉት ነገሮች ላይ የcheck and balance ክፍተት እንዳለ አመላክተዋል። የግብር መስሪያ ቤት ሰራተኞች እጅ ከፍንጅ ጉቦ ሲቀበሉ ወይም ሲያቀባብሉ/ሲስተላልፉ ተይዘው ለህግ ከቀረቡ በኋላ በነጋታዉ ተፈተው ከተማ ውስጥ ሲዝናኑ የሚታዩበትን አጋጣሚዎች በምሳሌነት አንስተዋል። ስለዚህም ኮሚሽኑ የራሱን ተቋም መፈተሽ አለበት፣ አደረጃጀቱም መስተካከል ይገባዋል ብለዋል።

ለዚህ ሙስና ስጋት መከሰት እንደ ምክንያት ከተነሱት ውስጥ የታክስ ባለሙያዎች የስነ-ምግባር ጉድለት፣ የግብር መኮንኖች የክፍያ (ደመወዝ) መጠናቸው ላይ እርካታ ማጣት (ይህም ብልሹ ባህሪ ውስጥ የመሰማራት ዝንባሌን መጨመር)፣ የቁጥጥርና ክትትል ማነስ/አለመኖር እና ዘመናዊ የግብር አሰባሰብ/አከፋፈል (E-file and E-payment) ለሁሉም አለመዳረሱ ይገኙበታል። በተጨማሪም ለመንግስት ደንቦች እና መመሪያዎች "አመቺ" ትርጓሜዎችን ለመስጠት ቀዳዳ መኖር፣ ከገቢያቸው (አቅማቸው) በላይ በሚኖሩ ሰራተኞች ላይ ጠንካራ የክትትል ስልት አለመኖር፣ ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ የግብር ሰብሳቢ ሰራተኞች ላይ የሚወሰኑ ቅጣቶች ከደረሰው ጥፋት ጋር ያልተመጣጠኑ መሆን፣ የጠቋሚ እና መረጃ ሰጭ (whistleblower) ጥበቃ ማዕቀፎች ደካማ መሆናቸዉ እንዲሁም የመንግስት ግዢን በቴክኖሎጂ (E-procurement) ያለመደገፍ ተጠቃሽ ናቸው።

<u>የስጋት ደረጃ</u>፦ ከላይ እንደተጠቀሰው ሂደቶችን ለማፋጠን ክፍያ እንደሚጠየቅ 65.7% የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች ተስማምተውበታል። በተጨማሪም ሌሎቹ የዚህ ሙስና ስጋት አመላካቾች (indicators) ከ60 በመቶ በላይ በሆኑ የመጠይቅ መላሾች ሙሉ ወይም መጠነኛ ስምምነት አግኝተዋል። እነዚህ ግኝቶች በቃለ-መጠይቅ መላሾችም ድጋፍ አግኝተዋል። ከዚህም በመነሳት የመከሰት ዕድሉ ከፍተኛ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል። አደጋው ከተከሰተ የታክስ ገቢ በእጅጉ ይቀንሳል፣ መንግስት ወጪዎችን ፋይናንስ ለማድረግ ሌሎች መንገዶችን እንዲፈልግ ያስገድደዋል፣ ይህም የበጀት ዘላቂነትን (fiscal sustainability) አደጋ ላይ ይጥላል። በታክስ ከፋዩ በኩል በፈቃደኝነት የታክስ ህጎችን እና ደንቦችን ማክበር ይቀንሳል። ህዝቡም በመንግስታዊ ተቋማት ላይ ያለውን እምነት ይሸረሽራል። ስለዚህ የጉዳቱ መጠን ከፍተኛ ነው። የመከሰት ዕድል እና የተፅእኖ ጥምረት የስጋቱን ደረጃ ከፍተኛ (ከባድ) ያደርገዋል።

በግብር ሰብሳቢ ባለሙያዎች እና በሌሎች ተዋናዮች (የሂሳብ ባለሙያዎች፣ ግብር ከፋዮች እንዲሁም ኦዲተሮች) መካከል ያለውን አላስፈላጊ ግንኙነቶችን መቁረጥ፣ የሠራተኛውን ስነ-ምግባር በሥልጠናዎች ማነፅ፣ ዘመናዊ አሰራሮችን ማስፋፋት እና ሁሉም እንዲጠቀም ማስገደድ፣ የግብር ሰራተኞችን ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ማራኪ እና ተወዳዳሪ ማድረግ፣ ለጠቋሚዎች የሥራና የሕይወት ዋስትና/ከለላ የሚሰጥ ጠንካራ ሕጋዊ ማዕቀፍ ተግባራዊ ማድረግ፣ እንዲሁም በጥፋተኞች ላይ አስተማሪና ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ለዚህ የሙስና ስጋት መፍትሔ ናቸው ብለን እናምናለን።

ክፍል 5፡- የጥናቱ ግኝቶች ማጠቃለያ (Summary)

የዚህ ጥናት ዓላማ በገቢዎች ዘርፍ ሥር ባሉ ተቋማት (በገቢዎችና ጉምሩክ) ውስጥ የሙስና ስጋት ጥናት በማካሄድ ሙስናን ለመቀነስ ምክረ-ሃሳብ መስጠት ነው፡፡ ጥናቱ ባለአምስት ደረጃዎች የሙስና ሰጋት ዳሰሳ ጥናት ሂደት ተከትሎ የተሰራ ነው፡፡ በነዚህ ደረጃዎች መሰረት የሙስና ስጋቶች እና ብልሹ አሰራሮች ተለይተዋል፣ የተለዩት የሙስና ስጋቶች ተተንትነውና በግምገማ ደረጃ ወጥቶላቸው ከነመፍትሄያቸው በጥልቀት ተሰንደዋል፡፡ የጥናቱ ግኝቶች ማጠቃለያ (Summary) በሰንጠረዥ 4 እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4፦ የጥናቱ ግኝቶች ማጠቃለያ

የሙስና ስጋት	የመከሰት እድል	የጉዳት መጠን	ለመከሰቱ ምክንያቶች	ሊወሰዱ የሚገቡ ማሻሻያ እርምጃዎች
የዋጋ አተማመን መመሪያን መሰረት ያላደረገ ዋጋ መወሰን	ከፍተኛ	ከፍተኛ	• የመነሻ ዋጋ ያልተቀመጠላቸው በርካታ ዕቃዎች መኖር • በስራ መብዛት/ግዙፍነት ምክንያት የክትትልና የቁጥጥር መላላት ወይም ማነስ • በቂ ሰራተኛ አለመኖር፣ ያሉትም ላይ አቅም/ልምድ/ክህሎት ማነስ • የግል ጥቅም ፍለጋ (በድርድር) • እርምጃ የሚወስድ አካል ኮሚትመንት ማነስ እና ቅጣቱን ለማቅለል በቀረቤታ መወሰን • ጥፋቱና በአጥፊዎች ላይ የሚወሰደው የዲሲፕሊን እርምጃ የተመጣጠኑ አለመሆን ሪስክ ለመውሰድ መጋበዙ • ቀረጥና ታክሳቸው በክብደት ላይ	• ተደጋጋሚ ችግር የሚገኝባቸውን ዕቃዎች በመለየት የመነሻ ዋጋ መትከል • የቅርብ ሀላፊ ክትትልን ማጠናከር እንዲሁም የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሽፋንን ማሳደግ፣ ወቅታዊ እና ተደራሽ ማድረግ • አደጋው ከመከሰቱ በፊት ሪስክን መሰረት ያደረገ የመከላከል ስራ መስራት • አቅም ለማሳደግ መደበኛ ስልጠና መስጠት • ለባለሙያዎች ተገቢ ጥቅም (ኢንሴንቲቭ) መስጠት • አመለካከትን ለመቀየር የተጠናከረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት • ዋጋ አሳንሶ ጥቅም ለማግኘት ሆን ብለው የሚያደርጉን ተጠያቂ ማድረግ፣ አስተማሪና ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የዲሲፕሊን እርምጃም መውሰድ • ባትሎአድ ዲጂታል የሆነ ተአማኒ የምድር ሚዛን በየደረቅ ወደብ እንዲተክል ማድረግ፣ እስከዛው ግን

			ተመስርቶ ለሚሰሩ ዕቃዎች (ለምሳሌ ብረታ ብረት) አስመጪው ከጉምሩክ ሰራተኛ ጋር ምድር ሚዛን ያላቸው ድርጅቶች ጋር እየወሰደ ሲያስመዝን የመሞዳሞድ አጋጣሚ መፈጠር • ደረቅ ወደቦችን የሚያስተዳድረው ባትሎአድ የሚዛን ፋሲሊቲ የሌለው መሆኑ	አስመጪው ከጉምሩክ ሰራተኛ ጋር ምድር ሚዛን ያላቸው ድርጅቶች ጋር እየወሰደ ሲያስመዝን ሙስና እንዳይሰራ የቁጥጥር ስርአት መዘርጋት (ቼክ ኤንድ ባላንስ)
ዕቃዎችን የታሪፍ አጣጣል መመሪያን ያላማከለ ታሪፍ ላይ መመደብ	ከፍተኛ	ከፍተኛ	• የታሪፎች በየጊዜው መቀያየር • በገንዘብ ሚኒስቴርና በጉምሩክ ኮሚሽን መካከል የቅንጅት ክፍተት (የታሪፍ ማሻሻያዎች በገንዘብ ሚኒስቴር ከወጡ በኋላ በጉምሩክ ሲስተም (ECMS) ውስጥ ገብተው ተግባራዊ እስከሚደረጉ ድረስ የቀናት ልዩነት መኖር) • የማትጊያና ማቆያ ስርዓት ባለመኖሩ ልምድ ያላቸው ኦፊሰርስ ከስራ መልቀቅ • በቂ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል የማግኘት ችግር፣ አዲሶቹ ደግሞ በቶሎ አዳፕት ማድረግ መቸገራቸው (አቅም እና ልምድ ማነስ) • የስነ-ምግባር ችግር (ሆን ብሎ በዝቅተኛ የታሪፍ መደብ መመደብ፦ በተለይ ከጨርቃ ጨርቅ ጋር በተገናኘ)	• በገንዘብ ሚኒስቴርና በጉምሩክ ኮሚሽን መካከል ያለውን ቅንጅት በማጠናከር የታሪፍ ማሻሻያዎችን በወቅቱ (ሳይዘገይ) ተግባራዊ ማድረግ • የማትጊያና ማቆያ ስርዓት መዘርጋት (አቅም በፈቀደ መጠን) • የባለሙያዎችን የሙያ ክህሎት በመደበኛ እና ወቅታዊ ስልጠና ማሳደግ • በየዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በልዩ ፓኬጅ (ኢንሴንቲቭ) ቀጥሮ በቦታው ላይ መመደብ • በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር (የተጠናከረ የኦዲት ስርአት መዘርጋት) • ለአመራሮችና ሠራተኞች ጥራትና ተገቢነት ያለዉ የሥነ-ምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበቻ ሥልጠና መደበኛ የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ መስጠት • አጥፊዎችን ተከታትሎ ወደ ሕግ የማቅረብ ስርአትን ማጠናከር
የኢንሹራንስ፣ የባህር ትራንስፖርት እና ሌሎች ወጪዎችን (IFO) በተመኑ መሰረት አለማስላት	ከፍተኛ	ዝቅተኛ	• ኢምንት ነው በሚል በድህረ ዕቃ አወጣጥ ብዙም ትኩረት አለማግኘት • በንዝህላልነት (ignorance) የIFO ወጪዎችን ሳያካትቱ የሚሰሩ ባለሙያዎች መኖር	• ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዋጋ ላይ ክትትል እንደሚያደርገው ሁሉ IFO ላይም ትኩረት ሰጥቶ ክትትል ማድረግ • አንደር-ኢንቮይሲንግ የፈጠረው ክፍተት እስከሚስተካከል ድረስ ጉምሩክ ሚኒመም ኢንሹራንስ ቫልዩ አስቀምጦ ቀረጥና ታክስ ቢያሰላ

የወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓትን አለአግባብ መጠቀም	ዝቅተኛ	ከፍተኛ	• የቁጥጥር እና ክትትል መላላት ወይም ማነስ • የቀረጥ ነፃ መብት ከመሰረቱ በተለያዩ አካላት የሚሰጥ ከመሆኑ አንፃር በአግባቡ መተግበራቸውን የሚከታተል፣ የሚደግፍና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚያስተባብር የረባ ቁመና ያለው አደረጃጀት አለመኖር • አብዛኞዎቹ የቫውቸር ተጠቃሚዎች እንዱስትሪ ፓርክ የሚገኙ አምራቾች እንደመሆናቸው መጠን፣ በኢንዱስትሪ ልማት ኮርፖሬሽን እና በጉምሩክ መካከል በቂ ቅንጅት አለመኖር • ስነ-ምግባር ችግር (ሪስክ ወስዶ አግባብ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት)	• የቁጥጥርና ክትትል ስርአቱን ማጠናከር • የቀረጥ ነፃ መብቶች በአግባቡ መተግበራቸውን የሚከታተል፣ የሚደግፍና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚያስተባብር አደረጃጀት ተግባራዊ ማድረግ • በኢንዱስትሪ ልማት ኮርፖሬሽን እና በጉምሩክ ኮሚሽን መካከል ያለውን ቅንጅት ማጠናከር • በወጪ ዕቃዎች ላይ ትክክለኛ የዋጋ ዳታ ቤዝ በማደራጀት የተመረቱ ዕቃዎች እንደየጥራት ደረጃቸው ተለይተው ወደሚመለከታቸው ሀገሮች በትክክለኛ ዋጋ እንዲወጡ የሚደረግበትን አሰራር መቅረፅ
የተገልጋዮች ስምምነት ቻርተርን ያላማከለ የገቢ ዕቃዎች ፍተሻ (የተገልጋዮች ስምምነት ቻርተር ላይ በተቀመጠው የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት ፍተሻ አለማከናወን)	ዝቅተኛ	ከፍተኛ	• የክትትልና ቁጥጥር ማነስ • የሰራተኞች አቅም ክፍተት፣ ፍራቻ እና በራስ አለመተማመን • የስራ ብዛትና ያለው የሰው ሀይል አለመመጣጠን • የስነ-ምግባር ችግር (የአገልግሎት አሰጣጡን በማጓተት የድርድርና የሌብነት ስራ ላይ ለመሰማራት) • የቻርተሩ የዕቃዎችን ባሕሪ ከግምት ውስጥ አለማስገባት (ለምሳሌ ለቁሳቁስ እና ማሽነሪ ተመሳሳይ ስታንዳርድ) • ልዩ ሙያዊ ዕውቀት የሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች መኖር (ለምሳሌ ኬሚካል ኮምፖዚሽኖች)	• ቀልጣፋና ፍትሀዊ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት ይቻል ዘንድ ሰነድ ከተመራበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚደረገውን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር • የፍተሻ ሰራተኞች የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን በመደበኛ መልክ እንዲያገኙ ማድረግ • ለፍተሻ ልዩ ሙያዊ ዕውቀት የሚያስፈልጋቸውን ዕቃዎች ለይቶ በመስኩ ባለሙያተኞችን ማሰልጠን፣ ገበያ ላይ ከተገኙም መቅጠር • ቻርተሩን ማሻሻል (የዕቃዎችን ባሕሪ ከግምት ዉስጥ በማስገባት) • ያለበቂ ምክንያት የፍተሻ ሂደቱን የሚያጓትቱ እና በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የማይፈትሹ ሰራተኞች ላይ የተጠናከረ እርምጃ መውሰድ

ታክስ ያልተከፈለባቸው ዕቃዎች ከህጋዊዎቹ ጋር ተቀላቅለው መግባት/መውጣት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	• በድንገተኛ ፍተሻ እና ኢንተለጀንስ ባለሙያዎች፦ 1) የስጋት ደረጃቸው መካከለኛና ዝቅተኛ በሆኑ የቀረጥ ነፃ እቃዎች ላይ ትኩረት አለማድረግ 2) ዕቃዎች ለንግድ አላማ የማይውሉ ናቸው ብሎ በማሰብ ትኩረት አለመስጠት 3) የወጪ ንግድ ዕቃዎች ላይ የላላ ቁጥጥር እና ክትትል መኖር • የኢንተሊጀንስና የድንገተኛ ፍተሻ መረጃ በሲስተም የተደገፈ አለመሆን • የስነ-ምግባር ጥሰት (ሆን ብሎ የማጭበርበር ተግባር)	• ከቀረጥ ነፃ በሚገቡ እቃዎች ላይ ድንገተኛ ፍተሻ የስጋት ደረጃቸው መካከለኛና ዝቅተኛ የሆኑት ላይም ቢያተኩር • ድንገተኛ እና ኢንተለጀንስ ንግድ ያልሆኑ ዕቃዎች እንዲሁም ወጪ ዕቃዎች ላይም ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ ቢደረግ • ኢንተለጀንስ ባለሙያዎች ተገቢ የመረጃና የክትትል ስራ ዕቃው ምንም ይሁን ምን በተጠናከረ መልኩ ቢሰሩ • የኢንተለጀንስና የድንገተኛ ፍተሻ መረጃ በሲስተም የተደገፈ ማድረግ • ሆን ተብሎ የሚደረግን የማጭበርበር ተግባር ቀድሞ ለመከላከል ለተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች ጥራትና ተገቢነት ያለዉ የሥነ-ምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበቻ ሥልጠና መደበኛ አሠራር ሥርዓት ዘርግቶ መስጠት
በመመሪያው የጊዜ ገደብ መሰረት ለአቤቱታዎች ውሳኔ አለመስጠት	መካከለኛ	መካከለኛ	• የአቤቱታ ማጣራት ሂደት ውስብስብነት • በአቤቱታ አቅራቢዎች በኩል አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችና መረጃዎችን ማቅረብ ላይ ያለ ክፍተት	• የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍልን አቅም እና ብቃት ማዳበር • ውሳኔ አሰጣጥን የሚያቀላጥፉ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎችና መረጃዎችን በተመለከተ ለአቤቱታ አቅራቢዎች በቂ ግንዛቤ መስጠት
መመሪያን የጣሰ በጊዜያዊነት ከሀገር የወጡ ወይም የገቡ ዕቃዎች አስተዳደር	ዝቅተኛ	ከፍተኛ	• የገቢ ተሰብሳቢና ዋስትና ሒሳቦች አስተዳደር የስራ ክፍል ተከታትሎ የማስፈጸም ክፍተት • የቁጥጥር መላላት • ተገቢ ሰነዶችን አስቀርቦ ስራን በተገቢው መንገድ አለመስራት (ignorance) • በዋስትና አስተዳደር ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች ክህሎት ማነስ (የማይሆኑ ሰነዶች ቀርበው ተሰርቶ ሊሆን ስለሚችል) • ስነ-ምግባር ችግር (ሰራተኛው ሪስክ ወስዶ በድርድር አድርጎት ሊሆን	• የገቢ ተሰብሳቢና ዋስትና ሒሳቦች አስተዳደር የስራ ክፍል ተከታትሎ የማስፈጸም አቅሙን ማሳደግ • የክትትል እና ቁጥጥር ስርአቱን ማጠናከር (በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ለሌላ አገልግሎት እንዳይውሉ) • ለሰራተኞች የክህሎት ማበልፀግያ ስልጠና መስጠት • ህገወጥ ስራ ላይ በተሰማሩ ሰራተኞች ላይ አስተማሪ የሆነ እርምጃ መውሰድ • ዕቃዎች በጊዜያዊነት ሲገቡና ሲወጡ በመግቢያ በሮች ላይ በምን መልኩ መስተናገድ እንዳለባቸው የሚገልፅ መመሪያ/ደንብ ነድፎ በስራ ላይ ማዋል

			ስለሚችል) • ዕቃዎች በጊዜያዊነት ሲገቡና ሲወጡ በመግቢያ በሮች ላይ በምን መንገድ መስተናገድ እንዳለባቸው የሚገልፅ ወጥነት ያለው አሰራር አለመኖር	
ሰነድ አልባ እና ገደብ/ክልከላ የተደረገባቸውን ዕቃዎች በመመሳጠር በኬላ ማሳለፍ	መካከለኛ	ከፍተኛ	• ኬላ አካባቢ ጠንካራ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር • የስነ-ምግባር ችግር • የካርጎ ትራኪንግ/ጂፒኤስ ቴክኖሎጂ በስራ ላይ አለመዋል • የመኪና ቦዲ ፓርቶችን ለቅሸባ እንዲያመች በተራቀቀ መንገድ የመገጣጠም ሕገ-ወጥ ተግባር • የኮንትሮባንድ ንግድን የመከላከል ባህል በህብረተሰቡ ዘንድ አለመዳበር	• ኬላዎች አካባቢ ጠንካራ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት • ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ቀጣይነት ያለዉ የህገ-ወጥ ንግድና የኮንትሮባንድ መከላከል ስልት ቀይሶ መተግበር • የኮንትሮባንድ ንግድን የመከላከል ባህል እንዲዳብር ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በተጠናከረ መልኩ መስጠት • ካርጎ ትራኪንግ/ጂፒኤስ ቴክኖሎጂን መጠቀም • የጉምሩክ ማህተሞችን (customs seals) አስመስለው በመስራት የቅሸባ ተግባር የሚፈጽሙት ላይ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ
በስልጣን አላግባብ በመገልገል (በመጠቀም) ታክስ/ግብር መሰወር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	• የግብር ከፋዮች የግብር ሕጎችና አካሄዶች እውቀት ማነስ እንደ ክፍተት በመጠቀም የግል ጥቅምን ለማሳካት የሚደረግ ሕገ-ወጥ ተግባር • የታክስ አሰባሰብ ስርአት በቴክኖሎጂ አለመደገፍ (በተለይ በክልል ታክስ ስብሰባ ሂደት) • በታክስ ግመታ ወቅት ባለሱቆች ሱቁን ባዶ ስለሚያደርጉት ገማች ኮሚቴው ከባለሱቁ ጋር በመመሳጠር ባለችው ነገር ላይ ግምት መጣል (በጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች) • የታክስ ግመታ ባለሙያው ከግብር ከፋዩ ጋር በመመሳጠር የሚከፈለውን ግብር ዝቅ በማድረግ መወሰን	• የግብር ከፋዩን ስነ-ምግባር እና የታክስ ህጎችና ደንቦች ክህሎት ማስጨበጥ ላይ አተኩሮ መስራት እና የቁጥጥር ስርአትን ማጠንከር • የታክስ አሰባሰብ ስርአትን በቴክኖሎጂ መደገፍ (ማዘመን) እና ከባንክ ሲስተም ጋር ማገናኘት • በግብር ሰብሳቢ ባለሙያዎች እና ሌሎች (የሂሳብ ባለሙያዎች፣ ግብር ከፋዮች እንዲሁም ኦዲተሮች) መካከል ያለውን አላስፈላጊ ግንኙነቶች መቁረጥ፣ • ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት (ነፃ እና እፎይታ ፈቃድ ሰጪዎች) ጋር ተባብሮ/ተናቦ መስራት • የግብርን ሀገራዊ ፋይዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋት • ሠራተኛዉን መቆጣጠር

ጉቦ መቀበል	ከፍተኛ	ከፍተኛ	• የተወሰኑ የታክስ ባለሙያዎች/ ሰራተኞች የሥነ-ምግባር ችግር • የቁጥጥር መላላት/አለመኖር • ዘመናዊ የግብር አሰባሰብ/አከፋፈል ለሁለም አለመዳረሱ (E-file and E-payment) • ከደንበኛ ሰነድ ላይ ስህተት በመፈለግ ብቻ ማተኮር እና ከባለጉዳዩ ጋር እልህ መያያዝ ችግር • ባለጉዳዩን አጣብቂኝ ዉስጥ በማስገባት ለጉቦ መደራደር	• በግብር ሰብሳቢ ባለሙያዎች እና ሌሎች (የሂሳብ ባለሙያዎች፣ ግብር ከፋዮች እንዲሁም ኦዲተሮች) መካከል ያለውን አላስፈላጊ ግንኙነቶችን መቁረጥ • የሠራተኛውን ሥነ-ምግባር በሥልጠናዎች ማነፅ • ዘመናዊ አሰራሮችን ማስፋፋት እና ሁሉም እንዲጠቀም ማስገደድ (E-Payment and E-file systems) • የሰራተኞችን ብዛት እና ክህሎት ከተገልጋዩ ብዛት/አይነት አንፃር ማስተካከል • ተጠያቂነትን ሥራ ላይ ማዋል
መንግስታዊ ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ያላግባብ መጠቀም	መካከለኛ	ከፍተኛ	• የሰነዶች አጠቃቀም በሚጠበቀው ልክ ዲጂታል አለመሆን እና በስራ ላይ የዋለውም ኮምፕሌክስ በመሆኑ ምክንያት በማኑዋል መገልገል • የታክስ መረጃ አያያዝ ስርዓት እና የቁጥጥር ስርአት በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ አለማድረግ • የሂሳብ ባለሙያዎች፣ የግብር ሰብሳቢዎች፣ የባለ-ሃብቶች፣ ኦዲተሮች፣ ወዘተ በመመሳጠር ሃሰተኛ/የተጭበረበረ ሰነድ በመጠቀም ማጭበርበር • የተቋሙ ሠራተኞች የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ዕዉቀት ማነስ • የንብረት አያያዝ እና ክትትል ችግር • የካሽ ሬጅስተር ያለዉ ሃያ አንድ ካራክተር በመሆኑ ለክትትልም ስለማያመች ለሀሰተኛ ሰነድ መበራከት ራሱን የቻለ አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ታይቷል፡፡	• የእሴት ታክሱን እውነተኛነት ለማወቅና ለመተግበር ዲጅታል የባንክ ሲስተም መጠቀም • የሰራተኖች የስነ-ምግባርና የሰነዶች አስተዳደር ሲስተም አጠቃቀም ክህሎት ላይ ጠንክሮ መስራት • የሂሳብ ባለሙያዎች፣ የግብር ሰብሳቢዎች እና የግብር ከፋዮች ህገ-ወጥ ትስስር/መመሳጠር መከታተልና እርምጃ መውሰድ (ቢያንስ የገቢዎች ተቋም የራሱን ግብር ስብሳቢ ባለሙያዎች መከታተል ይችላል)፣ • የግብር አሰባሰብ ሂደትን ከእጅ በጅ ወደ ቴክኖሎጂ መቀየር (በዞን እና ወረዳዎች ጭምር) • የግብርን ሀገራዊ ፋይዳ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት • ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት (ንግድ ቢሮ፣ ኢንቨስትመንት ቢሮ፣ ወዘተ) ጋር ተናቦ መስራት

ያላግባብ ጉዳይን ማጓተት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	• የተወሰኑ የታክስ ባለሙያዎች/ ሰራተኞች የስነ-ምግባር ችግር • የቁጥጥር ማነስ/አለመኖር • ዘመናዊ የግብር አሰባሰብ /አከፋፈል ለሁለም አለመዳረሱ (E-file and E-payment) • በየተቋማቱ ያለው የሰው ሃይል እና ባለጉዳዮች ቁጥጥር አለመመጣጠን • የመብራት እና የበይነ-መረብ (network) መቆራረጥ • የሰራተኞች ክህሎት ማነስ እና ተነሳሽነት ማጣት፣ • በሙከራ ስራ ያልታዩ እና ያልተፈተሹ ሲስተሞች ወደ ስራ መግባት • አዲስ ወደ ስራ እየገቡ ያሉ በሲስተም መካተት ያለባቸው የስራ ክፍሎችና ወረዳዎች አለመካተታቸው	• የሠራተኛውን ስነ-ምግባር በሥልጠናዎች ማነፅ • ጉዳዮችን በፍጥነት ለማስኬድ በተቀመጠው የዜግነት ቻርተር ስታንዳርድ መሠረት ሥራዎች በፍጥነት እንዲከናወኑ ማድረግ • ዘመናዊ አሰራሮችን ማስፋፋት እና ሁሉም እንዲጠቀም ማስገደድ (E-Payment and E-file systems) • የሰራተኞችን ብዛት እና ክህሎት ከተገልጋዩ ብዛት/አይነት አንፃር ማስተካከል • ተጠያቂነትን ሥራ ላይ ማዋል • የመብራት እና ኔትዎርክ መቆራረጥን ከሚመለከታቸዉ ባለ-ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ማስተካከል • የግዢ ሂደትን በቴክኖሎጂ (ኢ-ፕሮኪዩርመንት) መጠቀም • ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ መስራት
የመረጃ ደህንነት ስጋት	መካከለኛ	መካከለኛ	• አንዳንድ ጊዜ ግብር ከፋዩ እዳ እያለበት ከውስጥና ከውጪ በመመሳጠር ዕዳ እዳ የለበትም ተብሎ ከሲስተም ይጠፋለታል • የፌደራል ግብር መ/ቤት የመረጃ ቅብብሎሽ እጅግ ደካማ መሆኑ • መረጃ ተጠይቆ እንደማይቀርብ፣ SiGTAS ተመልከቱ እንደሚባልና ይሄ ደግሞ የተመላሽ ሥርዓት ላይ አንዱ እንቅፋት ነዉ • በሙከራ ስራ ያልታዩ እና ያልተፈተሹ ሲስተሞች ወደ ስራ መግባታቸዉ • ከሥራ የለቀቁ ሠራተኞችን አካዉንት ተከታትሎ አለመዝጋት • አዲስ ወደ ስራ እየገቡ ያሉ በሲስተም መካተት ያለባቸው የስራ ክፍሎችና ወረዳዎች አለመካተታቸው	• ሲግታስ ላይ ወደ ኋላ ሄዶ ገቢ ለመሰብሰብ፣ የሥራ ሂደቱ ካልፈቀደ ለዉጥ ማድረግ እንዳይቻል ማድረግ • ሁሉንም ስራዎች ዲጂታላይዝ ማድረግ • ስራዎችን ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር ኢንተርፌስ በመፍጠር በቴክኖሎጂ ማዘመን • የሰነዶች መጥፋት እንዳያጋጥም ዳታ ዌር ሀውስ (Data ware housing) ወይም ORDMS የሚባል የሲስተም ማሽን ገዝቶ ሰነዶች በሲስተም ላይ እየተጫኑ የሚቀመጡበትን ሁኔታ ለሁሉም ዞኖች፤ የከተማ መስተዳድሮችና ወረዳዎች ተደራሽ ማድረግ • ከሥራ የለቀቁ ሠራተኞችን አካዉንት ተከታትሎ መዝጋት

ሰንጠረዥ 5 ከላይ በሰንጠረዥ 4 የተገልፁት የሙስና ስጋቶች ሊሰጣቸው የሚገባውን የትኩረት አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡ የትኩረት ደረጃዎቹ በሶስት ቀለማት ተመላክተዋል፡- ቀይ ለከፍተኛ ትኩረት፣ ቢጫ ለመካከለኛ ትኩረት እንዲሁም አረንጓዴ ለዝቅተኛ ትኩረት፡፡ የትኩረት ደረጃው መሰረት ያደረገው የስጋቶቹን የመከሰት ዕድል እና ቢከሰቱ ሊያመጡት የሚችሉትን ተፅዕኖ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 5፡- የሙስና ስጋቶች ሊሰጣቸው የሚገባው የትኩረት ደረጃ

የሙስና ስጋት	የመከሰት ዕድል	የሚያስከትለው ተፅእኖ	የስጋት ደረጃ
የዋጋ አተማመን መመሪያን መሰረት ያላደረገ ዋጋ መወሰን	ከፍተኛ	ከፍተኛ	
ዕቃዎችን የታሪፍ አጣጣል መመሪያን ያላማከለ ታሪፍ ላይ መመደብ	ከፍተኛ	ከፍተኛ	
የኢንሹራንስ፣ የባህር ትራንስፖርት እና ሌሎች ወጪዎችን (IFO) በተመኑ መሰረት አለማስላት	ከፍተኛ	ዝቅተኛ	
የወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓትን አለአግባብ መጠቀም	ዝቅተኛ	ከፍተኛ	
የተገልጋዮች ስምምነት ቻርተርን ያላማከለ የገቢ ዕቃዎች ፍተሻ	ዝቅተኛ	ከፍተኛ	
ታክስ ያልተከፈለባቸው ዕቃዎች ከህጋዊዎቹ ጋር ተቀላቅለው መግባት/መውጣት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	
በመመሪያው የጊዜ ገደብ መሰረት ለአቤቱታዎች ውሳኔ አለመስጠት	መካከለኛ	መካከለኛ	
መመሪያን የጣሰ በጊዜያዊነት ከሀገር የወጡ ወይም የገቡ ዕቃዎች አስተዳደር	ዝቅተኛ	ከፍተኛ	
ሰነድ አልባ እና ገደብ/ክልከላ የተደረገባቸውን ዕቃዎች በመመሳጠር በኬላ ማሳለፍ	መካከለኛ	ከፍተኛ	
በስልጣን አላግባብ በመገልገል (በመጠቀም) ታክስ/ግብር መሰወር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	
ጉቦ መቀበል	ከፍተኛ	ከፍተኛ	
መንግስታዊ ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ያላግባብ መጠቀም	መካከለኛ	ከፍተኛ	
ያላግባብ ጉዳይን ማጓተት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	
የመረጃ ደህንነት ስጋት	መካከለኛ	መካከለኛ	

ማጣቀሻዎች (References)*

Child, D., Key Steps to Address Corruption in Tax and Customs, Bergen: U4 Anti-Corruption Resource Centre, Chr. Michelsen Institute (U4 Brief), 2008, https://www.u4.no/publications/key-steps-to-address-corruption-in-tax-and-customs.

Corruption Crimes Proclamation No. 881/2015, Addis Ababa, Ethiopia.

Ethiopian Revenues and Customs Authority, Ethiopian Customs Guide, March 2017.

Fjeldstad, Odd-Helge, Revenue Administration and Corruption, The U4 Utstein Anti-Corruption Resource Centre, Issue 2:2005, https://www.cmi.no/publications/file/2558-revenue-administration-and-corruption.pdf

Maíra Martini, Approaches to Curbing Corruption in Tax Administration in Africa, Transparency International, Number: 2014:11, June 2014, https://www.transparency.org/files/content/corruptionqas/Approaches_to_curbing_corruption_in_tax_administration_in_Africa_2014.pdf

Revised Federal Ethics and Anti-corruption Commission Proclamation No. 1236/2021, Addis Ababa, Ethiopia.

Transparency International, Corruption Risk Assessment and Management Approaches in the Public Sector, October 2015, https://knowledgehub.transparency.org/assets/uploads/helpdesk/Corruption_risk_assessment_and_management_approaches_in_the_public_sector_2015.pdf

United Nations Development Programme (UNDP), Fighting corruption to improve governance, DP(02)/F471, Feb. 1999.

United Nations Global Compact Office, A Guide for Anti-Corruption Risk Assessment, 2013, https://d306pr3pise04h.cloudfront.net/docs/issues_doc%2FAnti-orruption%2FRiskAssessmentGuide.pdf

United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC), State of Integrity: A Guide on Conducting Corruption Risk Assessments in Public Organizations, Vienna, 2020, https://www.unodc.org/documents/corruption/Publications/2020/State_of_Integrity_EN.pdf

World Customs Organization (WCO), Guide to Corruption Risk Mapping, 2015, http://www.wcoomd.org/-/media/wco/public/global/pdf/topics/integrity/instruments-and-tools/risk_mapping_guide_june_2015.pdf?la=en

*** ከየተቋማቱ ለጥናት የተጠቀምንባቸው ሰነዶች በጣም ብዙ በመሆናቸው በዝርዝር ውስጥ አልተካተቱም።**

አባሪ (annex)፦ በዳሰሳ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ትንተና

1. ከገቢዎች እና ጉምሩክ ተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች የተሰበሰበ መረጃ ትንተና

1.1 የምላሽ ሰጪዎች የስነ-ሕዝብ ባህሪያት (Demographic characteristics of respondents)

ምስል A1 የምላሽ ሰጪዎችን የሥነ-ሕዝብ ባህሪያት ስብጥር ይመለከታል፡፡ ለዳሰሳ ጥናት ምላሽ የሰጡ ሀላፊዎች እና ሰራተኞች በቁጥር 748 ሲሆኑ፣ 537 ከገቢዎች 211 ደግሞ ከጉምሩክ ተቋማት የተውጣጡ ናቸው፡፡ ወደ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት መላሾች ወንዶች ናቸው፡፡ ወደ ግማሽ የሚጠጉት የጥናቱ ተሳታፊዎች እድሜያቸው ከ 31 እስከ 40 አመት ሲሆን፣ ሰባት-አስረኛ የሚሆኑት ደግሞ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ አላቸው፡፡ በተጨማሪም 45% እና 24% መላሾች በቅደም ተከተል ከ 6-10 አመት እና ከ 11-15 አመት የአገልግሎት ዘመን አላቸው፡፡ ስለዚህም ምላሽ ሰጪዎች በእውቀት ላይ የተመሰረቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ሀሳባቸውን ለማጋራት በቂ እውቀት ነበራቸው ማለት እንችላለን፡፡



ምስል A1፦ የምላሽ ሰጪዎች የስነ-ሕዝብ ባህሪያት

1.2 የመረጃ ግልጽነት

የመረጃ ግልጽነትን በተመለከተ ለቀረቡት ጉዳዮች በአማካይ 62 በመቶ ተሳታፊዎች ተስማሚ (favourable) ምላሾች (እስማማለሁ/በመጠኑ እስማማለሁ) የሰጡ ሲሆን፣ ወደ 20 በመቶ የሚሆኑት ግን እንደማይስማሙ ገልጸዋል፡፡ የቀሩት መላሾች (18 በመቶ) ደግሞ ጉዳዩን በተመለከተ ምንም አይነት እዉቀት እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡

ተስማሚ ምላሾች ካገኙት ጉዳዮች መካከል፣ ወቅታዊና ዓመታዊ የተቋማቱ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት (91.6%)፣ የተቋማቱ ፖሊሲና ስትራቴጂክ ዕቅድ የመረጃ ግልጽነት (90.6%)፣ የተቋማቱ አዋጅ፤ ደንብ፤ መመሪያና ስታንዳርድ የመረጃ ግልጽነት (89.2%)፣ ወቅታዊና ዓመታዊ የተቋማቱ የበጀት አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት (71.8%)፣ እና ዓመታዊ የተቋማቱ የንብረት ቆጠራ ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት (60.6%) በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው። በአንጻሩ አሉታዊ ምላሽ ወደ አንድ-አራተኛ በሚሆኑ ምላሽ ሰጪዎች የተሰጠባቸው ደግሞ፣ በገለልተኛ አካል የተመዘነ ዓመታዊ የደንበኛ እርካታ ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት (27.8%)፣ ወቅታዊና ዓመታዊ የተቋማቱ የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት (27.7%)፣ የመንግሥት ዓመታዊ መደበኛና ካፒታል በጀት አጠቃቀም የመረጃ ግልጽነት (25.3%)፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር የመረጃ ግልጽነት (24.8%)፣ እና የፕሮጀክቶች በጀት የመረጃ ግልጽነት (24.3%) ናቸው። የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና በጀት የመረጃ ግልጽነትን በተመለከተ በቅደም ተከተል 35.5% እና 35.1% መላሾች ምንም አይነት እዉቀት እንደሌላቸው ገልጸዋል (ምስል A2ን ይመልከቱ)።



ምስል A2፦ የመረጃ ግልጽነትን በተመለከተ በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

1.3 ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ አሰራሮችና መመሪያዎች

አብላጫዎቹ መላሾች ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ አሰራሮችና መመሪያዎችን በተመለከተ በጎ ምላሽ ሰጥተዋል። በተለይም 82% የጥናቱ ተሳታፊዎች ተቋማቸው የአመራርና የሰራተኞች የስነ-ምግባር መመሪያ እንዳለው ሲገልጹ፣ 70.6 በመቶዎቹ ደግሞ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ በተቋማቸው ስትራቴጂክ ዕቅድ ዉስጥ ተካቷል ብለዋል። ሁለት-ሶስተኛ መላሾች በተቋማቸው ውስጥ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል መቋቋሙን ሲያረጋግጡ፣ ወደ 23 በመቶ የሚጠጉት ግን ይህ ክፍል ስለመቋቋሙ እንደማያውቁ ገልፀዋል (ሰንጠረዥ A1ን ይመልከቱ)።

በተቋማቸው ውስጥ በመልካም ስነ-ምግባር አርአያ የሆኑ አመራሮችንና ሠራተኞችን የመለየትና ዕውቅና የመስጠት አሠራር ሥርዓት እንደሌለ አንድ-ሶስታኛ የጥናቱ ተካፊዮች የገለጹ ሲሆን ፣ አንድ-አራተኛ የሚሆኑት (24.2%) ደግሞ ለተቋማቸው አመራሮችና ሠራተኞች ጥራትና ተገቢነት ያለዉ የስነ-ምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበቻ ሥልጠና መደበኛ አሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ አይሰጥም ብለዋል። በተጨማሪም አንድ-አምስተኛ መላሾች የተቋማቸው ሠራተኞች ተገልጋዩን ለማስተናገድ ቅንነትና ተዓማኒነት እንደሁም ከብልሹ ተግባራት የፀዱ ስለመሆናቸዉ የሚያረጋግጥ የአሠራር ሥርዓት የለም ብለዋል።

ሰንጠረዥ A1፦ ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ አሰራሮችና መመሪያዎችን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

አሰራሮች/መመሪያዎች	አዎ	በሂደት ላይ	የለም	አላውቅም
የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት ተቋቁሟል፡፡	67.5	5.9	3.8	22.8
የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ በተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዉስጥ ተካትቷል፡፡	70.6	10.5	4.0	14.9
ተቋሙ በስነ-ምግባር የታነፀ አመራር ግንባታ አሠራር ሥርዓት አለዉ፡፡	42.9	30.8	17.3	9.0
ተቋሙ በስነ-ምግባር የታነፀ ሰራተኛ ግንባታ አሠራር ሥርዓት አለዉ፡፡	42.7	32.6	16.0	8.6
ለተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞች ጥራትና ተገቢነት ያለዉ የስነ-ምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበቻ ሥልጠና መደበኛ አሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ይሰጣል፡፡	37.9	30.5	24.2	7.5
ተቋሙ የአመራርና የሰራተኞችን የስነ-ምግባር መመሪያ አለዉ፡፡	82.0	7.5	4.8	5.7
የተቋሙ ሠራተኞች ተገልጋዩን ለማስተናገድ ቅንነትና ተዓማኒነት እንደሁም ከብልሹ ተግባራት የጸዱ ስለመሆናቸዉ የሚያረጋግጥ አሠራር ሥርዓት አለ፡፡	43.4	24.7	20.1	11.8
በተቋሙ በመልካም ስነ-ምግባር አርአያ የሆኑ አመራሮችንና ሠራተኞችን የመለየትና ዕውቅና የመስጠት አሠራር ሥርዓት አለ፡፡	36.5	21.7	30.4	11.4
የተቋሙ አመራርና ሰራተኛ የመንግሥት የሥራ ሰዓትን ዉጤታማ አድርጎ የመጠቀም ምጣኔ ለመከታተል አሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡	55.8	25.7	11.9	6.6
በተቋሙ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበልና ተገቢዉን የእርምት እርምጃ ለመዉሰድ የተዘረጋ አሠራር ሥርዓት አለ፡፡	60.8	17.7	11.2	10.3
ተቋሙ በዉስጥና በዉጭ ኦዲተሮች የተለዩትን ግኝቶች የማረጋገጥና ተገቢዉን ማሻሻያ እርምጃ አሠራር ሥርዓት ዘርግቷል፡፡	54.8	19.9	9.6	15.7

1.4 የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል አቅምና ብቃት

ምስል A3 የተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን አቅምና ብቃት ይመለከታል፡፡ ይህንን ጉዳይ ለተመለከቱ ሀሳቦች አብላጫዎቹ ምላሽ ሰጪዎች ስምምነታቸውን ወይም መጠነኛ ስምምነታቸውን ገልጸዋል፡፡ በንጽጽር አነስተኛ የስምምነት ደረጃ ያገኘው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ሙስና እንዲቀንስና ስነ-ምግባር ጉድለት እንዲታረም አሠራር ሥርዓት፤ አቅምና ብቃት አጎልብቷል የሚለው ሀሳብ ነው፡፡ በተጨማሪም አንድ-አምስተኛ የጥናቱ ተሳታፊዎች የተቋማቸው የበላይ አመራር የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ምክረ-ሐሳቦችን መነሻ በማድረግ ተቋማዊ አሠራር ሥርዓት ግልጽነትን አሻሽሏል እንዲሁም የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ከተቋማቸው ሥራ ክፍሎች ጋር ትስስር፤ ትብብርና ቅንጅት በመፍጠር የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ተልዕኮ በብቃት ይወጣል በሚሉት ሀሳቦች ላይ እንደማይስማሙ የሰጡት መረጃ ያሳያል፡፡



ምስል A3፦ የተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን አቅምና ብቃት በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

1.5 ሙስናን ለመዋጋት ተነሳሽነት ፣ አቅም እና ብቃት

አብላጫዎቹ መላሾች ተቋማቸው ሙስናን ለመዋጋት ያለውን ተነሳሽነት ፣ አቅም እና ብቃት በተመለከተ በጎ ምላሻቸውን (ሙሉ ወይም ከፊል ስምምነታቸውን) ሰጥተዋል፡፡ በተለይም 86.1% መላሾች በተቋማቱ ያሉ ባለሙያዎች የሥራና የሙያ ስነ-ምግባር ያከብራሉ ብለው ያምናሉ፡፡ ሆኖም ግን ቢያንስ ከአምስት መላሾች አንዱ የበላይ፣ የመካከለኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ አመራሮች እንዲሁም ሰራተኞች ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸዉ በሚለው ሀሳብ አይስማማም (ሰንጠረዥ A2ን ይመልከቱ)፡፡

ሰንጠረዥ A2፦ የተቋማት አመራሮች እና ሰራተኞች ሙስናን ለመዋጋት ያላቸውን ተነሳሽነት ፣ አቅም እና ብቃት በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

ሙስናን ከመዋጋት ጋር ተያያዥ ጉዳዮች	እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	አልስማማም	አላውቅም
የአመራርና የሰራተኞችን የሥነምግባር ጉድለት ለመቆጣጠርና ለማረም የተቋሙ አመራር በቂ ግንዛቤና ተነሳሽነት አለዉ	36.0	42.3	17.1	4.6
የተቋሙ ሁሉም አመራሮችና ሰራተኞች በተልዕኮና ራዕይ የጋራ ግንዛቤ አላቸዉ	28.1	46.7	20.6	4.6
በተቋሙ ያሉ ባለሙያዎች የሥራና የሙያ ሥነምግባር ያከብራሉ	32.4	53.6	9.7	4.2
በተቋሙ ያታዊ ትንኮሳዎችንና ብልሹ ሥነምግባር ተጋላጭነትን ለመከላከል የተዘረጋ የጎለበተ የአሠራር ሥርዓት አለ	28.8	35.5	16.3	19.4
የተቋሙ የበላይ አመራር ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አለው	31.8	39.5	18.5	10.2
የተቋሙ የመካከለኛ አመራሮች ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸዉ	24.3	44.1	21.1	10.3
የተቋሙ የመጀመሪያ ደረጃ አመራሮች ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸዉ	23.3	46.1	20.9	9.8
የተቋሙ ሰራተኞች ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸዉ	22.7	46.9	20.5	9.9

1.6 የሙስና ተግባራት መረጃን የማመንጨት አቅም እና ብቃት

ሰንጠረዥ A3 የተቋማት የሙስና ተግባራት መረጃን የማመንጨት አቅም እና ብቃት ይመለከታል፡፡ የተቋማቱ የበላይ አመራር ጥቆማዎችን ለመቀበልና ውሳኔ ለመስጠት ያለው ዝግጁነት እና ተነሳሽነት እንዲሁም ተቋማቱ የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ አለማክበር ስለሚያስከትለዉ ቅጣት የፈጠሩት ግንዛቤ ከ80% በላይ በሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች በጎ ምላሽ አግኝተዋል (እስማማለሁ/በመጠኑ እስማማለሁ)፡፡ ሰባት-አስረኛ መላሾች ደግሞ ተቋማቱ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን በማደራጀት ለኮሚሽኑ የማቅረብ አቅም እና ብቃት እንዳላቸው፣ እንዲሁም ተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እንዲያቀርቡ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እንደሚሰሩ በሙሉ ወይም በከፊል ይስማማሉ፡፡

አሉታዊ ምላሾች (አልስማማም) ከተሰጠባቸው ጉዳዮች መካከል፣ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያግዙ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን ክለቦችንና ንቅናቄዎችን የመፍጠር ስራ (38.2%)፣ ጠቋሚዎች የሥራና የሕይወት ዋስትና ከላለ/ጥበቃ እንዲሰጣቸው የሚደረግ ክትትልና ድጋፍ (32.7%)፣ የሙስና መረጃ ጥቆማዎችን በቴክኖሎጂ አማራጮች የማከናወን ስራ (30.0%)፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አፈጻጸም ከሙስና እና ብልሹ ተግባር የፀዳ ስለመሆኑ ጥቆማ የመቀበል እና የሕዝብና የባለድርሻ አካላትን አስተያየት የመሰብሰብ፤ የመተንተንና ማሻሻያ እርምጃዎችን የመዉሰድ አሠራር (22.1%)፣ እንዲሁም ሙስና እና ብልሹ ተግባራት መረጃ ጥቆማ አቅርቦትና የጠቋሚዎች የማበረታቻ አሠራር (21.8%) በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ A3፦ የተቋማት የሙስና ተግባራትን መረጃ የማመንጨት አቅም እና ብቃት በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

የሙስና መረጃ/ጥቆማ ጋር ተያያዥ ጉዳዮች	እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	አልስማማም	አላውቅም
የተቋሙ የበላይ አመራር ጥቆማዎችን ለመቀበልና ውሳኔ ለመስጠት ዝግጁነት እና ተነሳሽነትና አለው	45.6	35.7	10.0	8.6
ተቋሙ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን በማደራጀት ለኮሚሽኑ የማቅረብ አቅም እና ብቃት አለው	32.1	36.9	12.7	18.2
ተቋሙ የተመዘበረ ሀብት በመረጃ ላይ በመመስረትና ክትትል በማድረግ ለማስመለስ ጥረት አድርጓል	21.3	27.8	17.7	33.2
ተቋሙ ጠቋሚዎች የሙስናና ብልሹ ተግባራትን ጥቆማ እንዲያቀርቡ የማበረታታትና የማነሳሳት ስራ ይሰራል	25.0	39.8	18.6	16.4
ተቋሙ ተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እንዲያቀርቡ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል	26.7	44.8	17.0	11.5
ተቋሙ ጠቋሚዎች የሥራና የሕይወት ዋስትና ከላለ/ጥበቃ እንዲሰጣቸው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል	11.0	19.5	32.7	36.8
በተቋሙ ተጨባጭ ሁኔታ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያግዙ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን ክለቦችንና ንቅናቄዎችን ፈጥሯል	11.2	27.2	38.2	23.4
ተቋሙ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አፈጻጸም ከሙስና እና ብልሹ ተግባር የጸዳ ስለመሆኑ ጥቆማ የመቀበል እና የሕዝብና የባለድርሻ አካላትን አስተያየት የመሰብሰብ፣ የመተንተንና ማሻሻያ እርምጃዎችን የመዉሰድ አሠራር ዘርግቷል	19.1	34.1	22.1	24.6
ተቋሙ ሙስና እና ብልሹ ተግባራት መረጃ ጥቆማ አቅርቦትና የጠቋሚዎች የማበረታቻ አሠራር ሥርዓት አለው	21.0	30.5	21.8	26.7
ተቋሙ የሙስና ተግባራት መረጃና ማስረጃ አቅርቦትና የፍትህ ዉሳኔ አሠጣጥ ሥርዓት አለው	23.5	35.3	19.6	21.7
ተቋሙ የሙስና መረጃ ጥቆማዎችን በቴክኖሎጂ አማራጮች የማከናወን ስራ ሰርቷል	16.5	22.0	30.0	31.5
ተቋሙ የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ አለማክበር ስለሚያስከትለዉ ቅጣት ግንዛቤ ሰጥቷል	48.1	33.0	12.0	6.8
ተቋሙ የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ ለጠቋሚዎች ስላሚያስገኘዉ ጥቅም ግንዛቤ ሰጥቷል	30.1	29.8	19.0	21.1

1.7 የጥቅም ግጭት

የጥቅም ግጭቶችን ለማስወገድ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች እና የማስጠንቀቂያ ስርዓት በተቋማቸው ውስጥ መዘርጋታቸውን ወደ 46% የሚጠጉት መላሾች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ይስማሙባቸዋል፡፡ ከአንድ-አራተኛ በጥቂት የሚበልጡት ግን በነዚህ ጉዳዮች አይስማሙም (ምስል A4ን ይመልከቱ)፡፡



ምስል A4፦ የጥቅም ግጭትን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

2. ከጉምሩክ ተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች የተሰበሰበ መረጃ ትንተና

2.1 ጥቆማ እና ለጠቋሚዎች ከለላ/ዋስተና

በተቋማቸው ዉስጥ የተጠረጠሩ ብልሹ ተግባራትን ሪፖርት ማድረግ ግዴታ መሆኑን፣ እንዲሁም ጥፋቶችን ወይም የተሳሳቱ ድርጊቶችን ሪፖርት ለማድረግ ተቋማቸው ፖሊሲዎችን፣ ሂደቶችን እና ዘዴዎችን ማውጣቱን በቅደም ተከተል 82.6% እና 57.9% መላሾች ሙሉ በሙሉ ወይም በመጠኑ ይስማሙበታል:: ሆኖም ግን አብላጫዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች (51.0%) ስህተቶችን/ጥፋቶችን ሪፖርት በማድረጋቸው ምክንያት ሰራተኞች በቀል እንደማይደርስባቸው ዋስትና አለ በሚለው ሀሳብ አይስማሙም:: በተጨማሪም 46.2% የጥናቱ ተሳታፊዎች በተቋማቸው ዉስጥ የተሳሳተ/ህገወጥ ስራ ቢሰሩ ሁሉም ሰራተኞች/ባለስልጣናት ደረጃቸው ምንም ይሁን ምን አንድ አይነት እግድ ወይም ቅጣት ይጣልባቸዋል በሚለው ሀሳብ ላይ እንደማይስማሙ የሰጡት መረጃ ያሳያል (ምስል A5ን ይመልከቱ)::



ምስል A5፦ የተሳሳቱ ድርጊቶችን ሪፖርት ከማድረግ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

2.2 የአስተዳደር ስርዓቶች ዘመናዊነት እና አውቶሜሽን

ወደ 80% የሚጠጉ መላሾች በተቋማቸው ውስጥ የአስተዳደር ስርዓቶችን እና ሂደቶችን በተከታታይ የመገምገም እና የማዘመን ሂደት እንዳለ በሙሉ ወይም በከፊል ይስማማሉ:: በአንፃሩ 19% የጥናቱ ተሳታፊዎች አውቶማቲክ የክፍያ ሥርዓቶች/ሲስተሞች ሊፈጥሩ የሚችሉትን የሙስና ስጋት ለመተንተን በተቋማቸው ውስጥ የስጋት ግምገማ ይደረጋል በሚለው ሀሳብ አይስማሙም:: ይህን ጉዳይ በተመለከተ አንድ-ሶስተኛ መላሾች እንዲሁም አውቶማቲክ ሊደረጉ በማይችሉት ሂደቶች ላይ ቁጥጥር እና ክትትል ስለመደረጉ 31.3% መላሾች ምንም እንደማያውቁ መረጃው ያሳያል::



ምስል A6፦ የስርአት ማዘመን እና አውቶማቲክ ሲስተሞችን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

2.3 የሙስና ስጋቶች

2.3.1 ከክሊራንስ በፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች

ምስል A7 ከክሊራንስ በፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን ይመለከታል። በጉምሩክ የስራ ሂደት ውስጥ ከክሊራንስ በፊት ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብለው ከተዘረዘሩት የሙስና ስጋቶች መካከል የሸቀጦች ከዋጋ በታች ትመና ተግባር፣ ለሙስና ድርድር ተብሎ አካላዊ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ ከበቂ በላይ ወይም ከልክ ያለፈ የምርመራ/ቁጥጥር ተግባር፣ በማኒፌስት ላይ የተዘረዘሩ አንዳንድ ጭነቶች ዲክሌር አለመደረጋቸውን የመሸሸግ ተግባር፣ የሸቀጦች ዋጋ ትመና በሚገመገምበት ጊዜ የሰነዶችን ሂደት ለማፋጠን አግባብ ያልሆነ ክፍያ የመቀበል/የመጠየቅ ተግባር፣ እና የሸቀጦች ዋጋ ምደባ በሚገመገምበት ጊዜ የሰነዶችን ሂደት ለማፋጠን አግባብ ያልሆነ ክፍያ የመቀበል/የመጠየቅ ተግባር በቅደም ተከተል በ 72.7%፣ 60.6%፣ 59.5%፣ 55.1% እና 53.3% መላሾች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ስምምነት አግኝተዋል። በአንጻሩ በመጓጓዝ ላይ ያሉ እቃዎች (goods in transit) ለሃገር ውስጥ ፍጆታ ይለቀቃሉ፣ የምስክር ወረቀት ለምናባዊ ወጪ ንግድ ዕቃዎች ይሰጣል፣ እንዲሁም የዕቃዎች የተሳሳተ የስሪት/የተመረተበት አገር ዲክላራሲዮን ያለአግባብ ይፀድቃል የሚባሉትን የሙስና ስጋቶች አብላጫዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች አይስማሙበትም።

<u>መግለጫ</u> ፦ ከላይ የተገለጹት አሃዞች ስለጉዳዩ አናውቅም ያሉትን መላሾች አያካትቱም።



ምስል A7፦ ከክሊራንስ በፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

2.3.2 በክሊራንስ ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች

በጉምሩክ የስራ ሂደት ውስጥ በክሊራንስ ጊዜ ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብለው ከተዘረዘሩት የሙስና ስጋቶች መካከል በሙስና ድርድር እቃዎችን (cargo) ያለአግባብ በፍጥነት የመልቀቅ (release የማድረግ) ተግባር ከፍተኛ ድርሻውን በያዙት ምላሽ ሰጪዎች ስምምነት አላገኙም። ወደ አንድ-ሶስተኛ የሚሆኑት ደግሞ የእቃዎችን ክሊራንስ ለማፋጠን ክፍያ ይጠየቃል በሚባለው አይስማሙም። በአንፃሩ አንዳንድ ደንበኞች ከሌሎች የተለየ ልዩ መስተንግዶ በሙስና ድርድር (በክፍያ) ያገኛሉ ለሚለው ስጋት አብላጫዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ሙሉ ወይም መጠነኛ ስምምነታቸውን ገልጸዋል። ወደ 40% የሚጠጉት መላሾች ደግሞ የእቃዎች እና ሰነዶች ምርመራ ግኝቶች ላይ ባለስልጣናት አግባብ ያልሆነ ተፅእኖ ያደርጋሉ ብለው ያምናሉ (እስማማለሁ/በመጠኑ እስማማለሁ) (ምስል A8ን ይመልከቱ)።



ምስል A8፦ በክሊራንስ ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

2.3.3 ሌሎች ተያያዥ የሙስና ስጋቶች

ነጋዴዎች አስፈላጊውን የገቢ ንግድ ቀረጥ ሳይከፍሉ እቃዎችን ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲያውሉ የመልቀቅ፣ አስመጪዎች ከተስማሙበት መጠን በላይ እቃዎችን እንዲያወጡ የመፍቀድ፣ እና አስመጪዎች ከቀረጥ እፎይታ ተጠቃሚ የሆኑ ምርቶችን ላልተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ወይም ላልታለመው ዓላማ እንዲያስተላልፉ የመፍቀድ ተግባራት በአብላጫዎቹ መላሾች ስምምነት ያላገኙ የሙስና ስጋቶች ናቸው። በአንፃሩ ሙሉ ወይም መጠነኛ ስምምነት ካገኙት ስጋቶች መካከል፣ በጉምሩክ መስመር ላይ ባሉ የተለያዩ ቅርንጫፎች መካከል በቂ ቅንጅት ባለመኖሩ ምክንያት የሚከሰት አላስፈላጊ መዘግየት (62.9%)፣ የኮንትሮባንድ ተግባራትን አይቶ እንዳላዩ የማለፍ ተግባር (48.1%)፣ ከፍተኛ የታክስ/የቀረጥ ዋጋ ያላቸውን እቃዎች በዝቅተኛ ምድቦች የመተመን ስራ (47.9%)፣ እንዲሁም የሸቀጦችን ኮንትሮባንድ የማመቻቸት ወይም የማደራጀት ተግባር (35.9%) ተጠቃሽ ናቸው።

ሰንጠረዥ A4፦ የተቋማት የሙስና ስጋቶችን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

የሙስና ስጋቶች	እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	አልስማማም	አላውቅም
ነጋዴዎች አስፈላጊውን የገቢ ንግድ ቀረጥ (import duties) ሳይከፍሉ እቃዎችን ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲያውሉ ይለቀቅላቸዋል	4.3	13.7	59.2	22.7
አስመጪዎች ከቀረጥ እፎይታ ተጠቃሚ የሆኑ ምርቶችን ላልተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ወይም ላልታለመው ዓላማ እንዲያስተላልፉ ይፈቀዳል	3.3	13.3	56.9	26.5
አስመጪዎች ከተስማሙበት መጠን በላይ እቃዎችን እንዲያወጡ ይፈቀዳል	1.9	10.5	58.9	28.7
በጉምሩክ መስመር ላይ ባሉ የተለያዩ ቅርንጫፎች መካከል በቂ ቅንጅት ባለመኖሩ ምክንያት አላስፈላጊ መዘግየት ይፈጠራል	18.1	44.8	21.0	16.2
የኮንትሮባንድ ተግባራትን አይቶ እንዳላዩ የማለፍ ተግባር ይፈፀማል	13.3	34.8	23.8	28.1
የሸቀጦችን ኮንትሮባንድ የማመቻቸት ወይም የማደራጀት ተግባር ይፈፀማል	7.7	28.2	30.6	33.5
የተፎካካሪን የንግድ እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ ክፍያዎችን የመቀበል ተግባር ተስተውሏል	2.9	15.8	34.4	46.9
ፋይሎች እንዲጠፉ/እንዲሰወሩ ይደረጋል	5.3	13.0	39.1	42.5
ከፍተኛ የታክስ/የቀረጥ ዋጋ ያላቸውን እቃዎች በዝቅተኛ ምድቦች የመተመን ስራ ይሰራል	7.1	40.8	30.3	21.8

2.4 የሰው ሀብት አስተዳደር

ሰንጠረዥ A5 ከሰው ሀብት አስተዳደር ጋር ተያያዥ ጉዳዮችን ይመለከታል። ተስማሚ ምላሾች (እስማማለሁ/በመጠኑ እስማማለሁ) ከሶስት-አራተኛ በላይ በሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች ካገኙት ጉዳዮች መካከል፣ ሥነ ምግባርን እና ግልጽነትን የሚያራምዱ የውስጥ የሥራ ቅጥር ደንቦችና አሰራሮች መኖር (91.0%)፣ በቅድሚያ የተቀመጠ ግልጽ የሥራ ቅጥር መስፈርት መኖር (89.1%)፣ ሰራተኞች ለረጅም ጊዜ ተጋላጭ ቦታዎችን እንዳይዙ የሚደረግ የሰራተኞች ቦታ ዝውውር (78.7%)፣ እንዲሁም ከአፈጻጸም ምዘና ሥርዓት ጋር የተገናኘ ለሠራተኞች ግብረመልስ እና ሽልማት የመስጠት አሰራር (74.9%) በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው። በአንፃሩ ከደመወዝ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች አሉታዊ ምላሽ (አልስማማም) በበርካታ ተሳታፊዎች ተሰጥቶባቸዋል። ወደ 47%

የሚጠጉ የጥናቱ ተሳታፊዎች ደግሞ ግልፅ ያልሆኑ የምልመላ አሰራር እና ደንቦች አሉ ብለው ያምናሉ፡፡ በተጨማሪም ተቋማቱ በጥቂት ቁልፍ ግለሰቦች ላይ ከመጠን በላይ ጥገኛ እንዳይሆኑ ለማድረግ የሥልጣን መተካካት አለ የሚለው ሀሳብ 39.0% በሚሆኑት መላሾች ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ሰንጠረዥ A5፦ የተቋማት የሰው ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

የሰው ሀብት አስተዳደር ጋር ተያያዥ ጉዳዮች	እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	አልስማማም	አላውቅም
በቅድሚያ የተቀመጠ ግልጽ የሥራ ቅጥር መስፈርት አለ	69.7	19.4	7.1	3.8
ሥነ ምግባርን እና ግልጽነትን የሚያራምዱ የውስጥ የሥራ ቅጥር ደንቦችና አሰራሮች አሉ	59.7	31.3	5.7	3.3
ተቋሙ ለሰራተኞች ተመሳሳይ የስራ መደብ ካላቸው ከሌሎች የመንግስት ሴክተር ሠራተኞች ጋር ተነፃፃሪ ደሞዝ ይከፍላል	21.3	22.7	47.9	8.1
ተቋሙ ለሰራተኞች ተመሳሳይ የስራ መደብ ካላቸው ከሌሎች የግል ሴክተር ሠራተኞች ጋር ተነፃፃሪ ደሞዝ ይከፍላል	8.1	13.3	68.7	10.0
በተቋሙ ውስጥ ከአፈጻጸም ምዘና ሥርዓት ጋር የተገናኘ ለሠራተኞች ግብረመልስ እና ሽልማት ይሰጣል	28.4	46.4	21.3	3.8
ተቋሙ በጥቂት ቁልፍ ግለሰቦች ላይ ከመጠን በላይ ጥገኛ እንዳይሆን ለማድረግ የሥልጣን መተካካት አለ	11.4	38.6	39.0	11.0
ተቋሙ ሰራተኞች ለረጅም ጊዜ ተጋላጭ ቦታዎችን እንዳይዙ የሰራተኞችን ቦታ ያዘዋውራል	37.0	41.7	18.5	2.8
ምስጥራዊ የውሳኔ አሰጣጥን ጨምሮ ግልፅ ያልሆኑ የምልመላ አሰራር እና ደንቦች አሉ	15.4	31.3	30.3	23.1
የሥራ ቅጥር ደንቦችና አሰራሮችን የጣሰ የሰራተኞች ምልመላ ፣ መባረር፣ የደረጃ እድገት እና ዝውውር (ለምሳሌ የጓደኞች እና የዘመዶች ቅጥር) ይፈጸማል	18.2	24.9	34.4	22.5

3. ከገቢዎች ተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች የተሰበሰበ መረጃ ትንተና

3.1 ከግብር አሰባሰብ ፖሊሲ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች

በታክስ አሰባሰብ ሂደት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮችን መጠቆም የሚያስችሉ መጠይቆች ከጥናቱ ተሳታፊዎች ምላሽ ቀመር ውጤት ጋር በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመላክተዋል፡፡ በመጠኑ እስማማለሁ እና እስማማለሁ የሚሉት አማራጮች መስማማትን ስለሚገልፁ እስማማለሁ በሚል ቀመር ተተንትነዋል፡፡ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ለሁሉም መጠይቆች ከ57.8% በላይ መላሾች በችግሮቹ መከሰት በመጠኑ እስማማለሁ ወይም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ የተወሰኑትን በተናጥል ለማየት ያህል 'የተቋማቱ ሰራተኞች የታክስ መጠን አወሳሰን ላይ ያላቸው ስልጣን ከፍተኛ ነው' ለሚለው ጥያቄ 79.6% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች ችግሩ መኖሩን ተስማምተዋል፡፡ 'የተቋማት ተደራራቢ ወይም ግልጽ ያልሆነ ሀላፊነት (mandates) የደንቦችን አተገባበር እና ማስከበር ወጥነት (consistency) ያዳክማል' ለሚለው ጥያቄ 77.2% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች ችግሩ መኖሩን ተስማምተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው የችግሮቹ መከሰት ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡

ሰንጠረዥ A6፦ የግብር አሰባሰብ ፖሊሲን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

በታክስ ስብሰባ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ብልሹ አሰራሮች	እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	አልስማማም	አላውቅም
የግብር አሠራሮች እና ሂደቶች ውስብስብነት አላቸው፡፡	32.2	39.1	25.7	3.0
በታክስ አስተዳደር ውስብስብነት የተነሳ የህገወጥ ተግባራት የመጋለጥ እድል (chances of detection) ዝቅተኛ ነው፡፡	22.2	35.6	38.2	3.9
የተቋማቱ ሰራተኞች የታክስ መጠን አወሳሰን ላይ ያላቸው ስልጣን ከፍተኛ ነው፡፡	42.5	37.1	15.5	5.0
ህጎች እና ሂደቶች ውስብስብ በመሆናቸው ምክንያት በግብር ከፋይ እና በተቋሙ ሰራተኞች መካከል ያሉ ግንኙነቶች ብዙ ናቸው፡፡	31.5	42.3	23.6	2.6
የተቋማት ተደራራቢ ወይም ግልጽ ያልሆነ ሀላፊነት የደንቦችን አተገባበር እና ማስከበር ወጥነት ያዳክማል፡፡	43.9	33.3	16.6	6.1
በገቢዎች ሚኒስቴር እና የታክስ ፖሊሲን/ሕግ በሚያወጣው ገንዘብ ሚኒስቴር መካከል ግልጽ የሆነ የቅንጅት ሥራ የለም፡፡	16.0	32.2	27.2	24.6
ግልጽነትና ወጥነት የጎደላቸው የታክስ ህጎች በስርዓቱ ውስጥ ክፍተቶችን አስከትለዋል፡፡	36.1	39.7	16.0	8.2
የግብር አሠራሮችን እና ልምዶችን በተመለከተ በቂ መረጃ የማግኘት ችግር አለ፡፡	28.1	41.3	24.6	6.0
የመረጃ ሰጭ (whistleblower) ጥበቃ ማዕቀፎች ደካማ ናቸው፡፡	30.4	30.4	19.4	19.9

3.2 ፖለቲካዊ ተፅእና በግብር አስተዳደር ላይ

በዚህ ስር የፖለቲካ ተፅእኖ በግብር አስተዳደር ለመዳሰስ በሶስት ጥያቄዎች ተወክሎ በምስል A9 ከነመልስ ቀመሩ ተመላክቷል:: ለሶስቱም ጥያቄዎች የችግሩን መከሰት 'እስማማለሁ' ወይም 'በመጠኑ እስማማለሁ' ብለው ምላሽ የሰጡት 56.3%ና ከዚያ በታች ናቸው:: በተናጥል ስንመለከታቸው 'በታክስ ፖሊሲ አወጣጥ ላይ ያሉትን ክፍተቶች በመጠቀም ተጽእኖ ይደረጋል' ለሚለው ጥያቄ 56.3% የጥናቱ ተሳታፊዎች ችግሩ መኖሩን ተስማምተዉበታል:: 'በታክስ አስተዳደሩ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ፖለቲካዊ ጣልቃገብነት አለ' ለሚለው ጥያቄ እና 'በስራ ላይ የዋሉትን የታክስ ፖሊሲ እና ደንብ ለማስቀየር ባለሥልጣናት ላይ ጫና ይደረጋል' ለሚሉት ጥያቄዎች እስማማለሁ እና በመጠኑ እስማማለሁ በማለት ምላሽ የሰጡት የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅደም ተከተል 49.8% እና 36.7% ናቸው:: ይህ የሚያሳየው የድርጊቶቹ የመከሰት ዕድል መካከለኛ መሆኑን ነው::



ምስል A9፦ ፖለቲካዊ ተፅእኖን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

3.3 በሰራተኛ ቅጥርና አስተዳደር ያሉ ብልሹ አሰራሮች

በዚህ ስር ለጥናቱ በተመረጡ የገቢዎች ተቋማት ውስጥ በሰራተኛ ቅጥርና አስተዳደር ውስጥ ያሉ ብልሹ አሰራሮች ተመላክተዋል:: የምላሽ ቀመሩም በምስል A10 እንደሚታየው በስድስት ጥያቄዎች ተወክሎ ቀርቧል:: በዚሁ አኳኋን ለሁሉም ጥያቄዎች ከ55% በላይ የጥናቱ ተሳታፊዎች ችግሩ በከፍተኛ ደረጃ መኖሩን 'በመጠኑ እስማማለሁ' እና 'እስማማለሁ' በማለት አረጋግጠዋል:: የተወሰኑትን በተናጥል ለማየት 'ሰራተኛውን በአንድ የስራ አይነትና በአንድ የስራ አካባቢ ማቆየት' የሚለው ጥያቄ ትልቁን 'በመጠኑ እስማማለሁ' ወይም 'እስማማለሁ' የሚል ምላሽ (78.8%) ሲያገኝ፣ 'ብቃትን መሰረት ያላደረገ የሰራተኞ ምልመላ አለ' የሚለው ደግሞ በ55% መላሾች ሙሉ ወይም መጠነኛ ስምምነት አግኝቷል:: ይህ የሚያሳየው የችግሩ መከሰት እድል ከ50% በላይ መሆኑን ነው::



ምስል A10፦ በሰራተኛ ቅጥርና አስተዳደር ያሉ ብልሹ አሰራሮችን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

3.4 ከስራ አፈፃፀም እና ቁጥጥር ጋር ተያያዥ ጉዳዮች

በገቢዎች ተቋማት ውስጥ የገቢ አሰባሰብ ቁጥጥር ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመለክቱ ጥያቄዎች ከነምላሽ ቀመራቸው በሰንጠረዥ A7 ተመላክተዋል:: ችግር መሆናቸው ከ50% በላይ የጥናቱ ተሳታፊዎች የተስማሙባቸውን ጥያቄዎች ከነቀመራቸው ስንመለከት፦ ግልጽ እና ወቅታዊ የሆነ የቅሬታ አፈታት ስርአት አለመዘርጋት (50.1%)፣ ውጤታማ እና መደበኛ ክትትል ማነስ/አለመኖር በሙስና የተዘፈቁ ሳይታወቁ እንዲቆዩ በር ከፍቷል (65.6%)፣ የታክስ እዳዎችን የመለየት ድክመት አለ (61.8%)፣ የታክስ ወንጀሎችን የመፈተሽ እና የክስ ሂደት ድክመት አለ (63.3%)፣ ለመንግስት ደንቦች እና መመሪያዎች "አመቺ" ትርጓሜዎችን ("favourable" interpretations) ለመስጠት ቀዳዳ አለ (68.4%)፣ ግብር ሰብሳቢዎች ስለ ቀረጥ ህጎች/ኮድ ያላቸው እውቀት አናሳ ነው (65.9%)፣ በግብር መስሪያ ቤቱ በጣም የተወሳሰቡ ጉዳዮችን የማስተናገድ ልምድ ማነስ አለ (62.7%)፣ የተዘረጉት አውቶሜትድ ሲስተሞች ክፍተት (loopholes) አሉባቸው (66.1%)፣ አውቶሜትድ ሲስተሞችን በተመለከተ አመራሩ ሙያዊ ብቃት ይጎድለዋል (63.5%)፣ ትክክለኛ ያልሆኑ አሰራሮችን (irregularities) አይቶ እንዳላዩ የማለፍ ሁኔታ ይታያል/ታይቷል (55.5%) ናቸው::

ሰንጠረዥ A7፦ የስራ አፈፃፀም እና ቁጥጥርን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

	እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	እልስማማም	አላውቅም
የቁጥጥር እና የኦዲት ዘዴዎች ደረጃቸውን ያልጠበቁ ናቸው::	16.3	35.6	33.9	14.2
ደካማ የሰራተኞች፣ አቅርቦቶች (supplies) እና የበጀት አስተዳደር ቁጥጥር አለ::	20.3	41.5	25.1	13.0
ግልጽ እና ወቅታዊ የሆነ የቅሬታ አፈታት ስርአት አልተዘረጋም::	19.4	30.7	41.5	8.4
ውጤታማ እና መደበኛ ክትትል ማነስ/አለመኖር በሙስና የተዘፈቁ ሳይታወቁ እንዲቆዩ በር ከፍቷል::	34.3	31.3	22.7	11.7
የታክስ እዳዎችን የመለየት ድክመት አለ::	21.6	40.2	29.1	9.1
የታክስ ወንጀሎችን የመፈተሽ እና የክስ ሂደት ድክመት አለ::	28.1	35.2	22.5	14.2
ለመንግስት ደንቦች እና መመሪያዎች "አመቺ" ትርጓሜዎችን ለመስጠት ቀዳዳ አለ::	26.3	42.1	17.5	14.2
ግብር ሰብሳቢዎች ስለ ቀረጥ ህጎች/ኮድ ያላቸው እውቀት አናሳ ነው::	24.2	41.7	25.9	8.2
በግብር መስሪያ ቤቱ በጣም የተወሳሰቡ ጉዳዮችን የማስተናገድ ልምድ ማነስ አለ::	19.9	42.8	28.9	8.4
የተዘረጉት አውቶሜትድ ሲስተሞች ክፍተት (loopholes) አሉባቸው::	23.6	42.5	18.1	15.8
አውቶሜትድ ሲስተሞችን በተመለከተ አመራሩ ሙያዊ ብቃት ይጎድለዋል::	24.6	38.9	17.7	18.8
ትክክለኛ ያልሆኑ አሰራሮችን አይቶ እንዳላዩ የማለፍ ሁኔታ ይታያል/ታይቷል::	21.2	34.5	29.1	15.3

3.5 የሙስና ስጋቶችን የሚመለከት

በዚህ ስር በገቢዎች ተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመለክቱ ጥያቄዎች ከነ ምላሽ ቀመራቸው በሰንጠረዥ A8 ተመላክተዋል። የቀረቡት ክስተቶች ስጋት መሆናቸውን ከ59.7% በላይ የጥናቱ ተሳታፊዎች ተስማምተውባቸዋል። ከነዚህ ውስጥ የደንበኞችን የግብር ሕጎች እና አካሄዶች እውቀት ማነስ በመጠቀም ከመጠን ያለፈ (ከመደበኛ በላይ) ታክስ መተመን (74.4%)፣ ለሐሰተኛ ክፍያ ጥያቄዎች (ለምሳሌ ሐሰተኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ገንዘቦች) ክፍያ መፈፀም (69.1%) እንዲሁም የተወሳሰቡ አገልግሎቶችን ለማፋጠን ክፍያ መጠየቅ/መቀበል (65.7%) ጎልተው የወጡ ናቸው። ከዚህ የምንረዳው የተጠቀሱት የሙስና ስጋቶች የመከሰት እድላቸው ከፍተኛ መሆኑን ነው።

ሰንጠረዥ A8፦ የሙስና ስጋቶችን በተመለከተ የምላሽ ሰጪዎች ደረጃ አሰጣጦች (በመቶኛ)

	እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	እልስማማም	አላውቅም
ሰው ሰራሽ (artificial) መዘግየቶች በግብር ስርአት ውስጥ ተፈጥረዋል።	35.6	26.6	19.6	18.2
የተወሳሰቡ ሂደቶችን/አገልግሎቶችን ለማፋጠን ክፍያ ይጠየቃል።	30.7	35.0	19.7	14.5
ነፃ መሆን ለሚገባቸው አገልግሎቶች ክፍያ ይጠየቃል።	15.6	44.1	28.5	11.7
የደንበኞችን የግብር ሕጎች እና አካሄዶች እውቀት ማነስ በመጠቀም ከመጠን ያለፈ (ከመደበኛ በላይ) ታክስ ይተመናል።	35.9	38.5	16.9	8.6
ግብር ከፋዮች ገቢያቸውን ከትክክለኛው አሳንሰው ወይም ወጪዎችን ከመጠን በላይ አጋነው ሪፖርት እንዲያደርጉ ይመቻችላቸዋል።	31.3	31.7	23.0	14.0
ለሐሰተኛ ክፍያ ጥያቄዎች (ለምሳሌ ሐሰተኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ገንዘቦች) ክፍያ ይፈፀማል።	33.3	35.8	17.7	13.2